
ምስጋና

1. አቶ ወንድወሰን አሰፋ
   በእርምት ስራና በቅድመ ሕትመት ዝግጅት
   ሃሳብ በመስጠት፤
2. አቶ ፋንታሁን በየነ
   በተለያየ ማቴሪያል ስለተባበሩኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

ዋጋው 4 ብር

# ክፍል 1 ተቅዋመ ጽዮን

# ክፍል 2 ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤ



## ተቅዋመ ማህቶት

አዘጋጅ ገ/ዮሐንስ ገ/ማርያም (M.A.T)

ጥር፡1992

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

Beide-Mariam Ejigu
Feb 2014

ክፍል 1 ተቅዋመ ጽዮን
ክፍል 2 ቅኔ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ

አዘጋጅ ገ/ዮሐንስ ገ/ማርያም (M.A.T)

ጥር:1992

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ ገጽ


መግቢያ ....................................3

ምእራፍ 1 ተቅዋመ ጽዮን ....................5
ክፍል 1 ተቅዋም

ክፍል 2 ዘካሪያስ ተቅዋመ
ማሕቶትን አየ ..............................10

ሀ ተቅዋመ ማሕቶት በቅዱስ ኤፍሬም ........13

ለ ተቅዋመ ማሕቶት በቅዱስ ያሬድ ...........14

ም 2 /ጽዮን/ ...............................17

ቅ ኔና ሂደቱ ................................19

የቅ ኔ ትምህርት አጀማመር .....................27

የቅ ኔ ለተለያየ ስሜት

መግለጫ መሆን .............................32

ቅ ኔ በኢትዮጵያ

አድባራትና ገዳማት ..........................35


## መግቢያ

ይህ አነስተኛ መጽሐፍ በሁለት የተከፈለ ነው።

ክፍል አንድ "ተቅዋመ ጽዮን" በሚል ርዕስ ተጽፏል። ተቅዋመ ጽዮን ብሉይ ኪዳንን፣ ሐዲስ ኪዳንንና መጽሐፈ ሊቃውንትን መሠረት በማድረግ በተካሄደው ጥናት በመጠኑም ቢሆን ተገልጿል። ኦሪት ዘፀአት ም. 25፣31 ትንቢተ ዘካርያስ ም. 4፣2– 4 ተቅዋም (ተቅዋመ ማሕቶት) ለሚለው ቃል (ሐረግ) በመነሻነት ተወስዷል። ኦሪት ዘፀአት ም. 25 ስለ ታቦታት፣ ስለተለያዩ ዕቃዎች (ዕቃአት) ስለ ሕብስተ ገፅ ጠረጴዛና ስለ ተቅዋመ ማሕቶት የሚገልጽ ፍሬ ነገር የሰፈረበት ምዕራፍ ነው። ስለ መቅደስ መሠራትም ከእግዚአብሄር መታዘዙ በዚሁ ምዕራፍ ተጨማሪ ሆኖ ሠፍሯል። በመካከላቸው አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ (ወትገብር ሊተ መቅደሰ ወእትረአይ በላእሌሆሙ ዘፀ. 25፣8– 9) ከተጠቀሱት ንዋየ ቅድሳት መካከል ተቅየም (ተቅዋመ ማሕቶት) ተለይታ ለዚሁ ፅሁፍ በዋነኛነት ተወስዳለች። ምክንያቱም የተጠቀሱት ንዋየ ቅድሳት ጠፍተው ሲቀሩ (በባቢሎን ምርኮ ጊዜ) ተቅዋመ ማሕቶት ግን በቤተ መቅደስ ፍርስራሽ ውስጥ ልትገኝ ችላለች። ነቢዩ ዘካርያስም እሷን መሠረት ያደረገ ራዕይ አይቷል። የዘካርያስን ትንቢት ሊቃውንተቤተክርስቲያን ለምስጢረ ሥጋዌ ትምህርት ማስፋፍያ በማድረግ አብራርተውታል።

ክፍል ሁለት ደግሞ የቅኔን ታሪካዊ አመጣጥ የሚመለከት ነው። ቅኔ ማለት ምሥጋና ነው። የሰው ልጆች በእግዚአብሄር ፈቃድ መኖርን ያመለክታል። የቅኔ ትምህርት በዮሐንስ ገብላዊ ወይም በደቀእስጢፋ እንደተጀመረ የተለያዩ መዛግብት ያስረዳሉ። ቅኔ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል የምሥጢረ መጻሕፍት ምርምር ዘዴ ሆኖ ቆይቷል። ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ግን መሥመሩን ለቀቀ። የግለሰቦች ማወደሻ የፖለቲካ ማስፋፍያና የሥጋዊ ጥቅም ማስገኛ ከመሆን ሊያልፍ አልቻለም። ቅኔ በኢትዮጲያ በአራት የተከፈለ መንገድ ነበረው። የጎንጅ፣ የዋሸራ፣ የዋድላና የጎንደር በመባል ይታወቅ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

አሁን ያሁሉ የለም። ቅኔ የግዕዝ ቋንቋ መማርያ አይደለም። የግዕዝ ቋንቋ በሚገባ የተረዱ ምሁራን ለመጻሕፍት ምሥጢር ርቀት ይጠቀሙበት ነበር። እያደር ግን ቅኔ የግዕዝ መማርያ እየመሰላቸው ብዙዎች ቅኔን አበላሹት እነሱም ተበላሹ። በመጽሐፉ ውስጥ ብዙ ቁም ነገሮች በዝርዝር ተገልጸዋል። አንባቢያን ትኩረት ሠጥተው ፍሬ ነገሩን በመቅሰም እንደሚጠቀሙበት ተስፋ ይደረጋል።

አዘጋጂው።



## ምዕራፍ 1

## ተቅዋመ ጽዮን

### ክፍል 1. ተቅዋም ፡

ተቅዋም ማለት መቅረዝ ማብርያ፣ የመብራት ዕቃ፣ ቀንዲል የሚቆም የሚንጠለጠል ባለብዙ ዓፅቅ (ቅርንጫፍ) ማለት ነው። ተቅዋም በብሉይ ኪዳን ከፍተኛ ቦታ አላት። ሊቀ ነቢያት ሙሴ እግዚአብሄር በቃል እያነጋገረው ከተለያዩ ቁሳቁሶች ንዋየ ቅድሳትን ሠርቷል። ከንዋየ ቅድሳቱ አንዷ ተቅዋም ናት። ሙሴ ተቅዋምን ለመሥራት ከልዑል እግዚአብሄር የተሠጠውን መመሪያ በግዕዝና በአማርኛ ከዚህ በታች ሠፍሯል።

<u>በግዕዝ</u>:- ወትገብር ተቅዋመ ማሕቶታ እምወርቅ ንፁሕ ፍሕቆ ግብራ ተቅዋመ ማሕቶታ ዓምደ ወግብራቲሃ ወአዝኢሃ ወክበበ ርእሳ ወጽጌያቲሃ እምውስቴታ ይትገበር ሠለስቱ መዓሐዚሃ እለየሐውራ ምስለ አሐዱ ክበበ ርእሳ ዕጉዮ። ክማሁ ለስድስቲሆሙ ዓብራዕ ለእለይወፅኡ እምተቅዋመ ማሕቶት ወለተቅዋመ ማሕቶታ ወአሐዚሃ ዓርባዕቱ ወፅጌያቲ ወክበበ ርእሳ።

ክበበ ርእሳ ማዕከለ ክልኤቱ ዓብራዕ ክማሁ ለስድስቱዚ ዓብራው እለይወፅኡ እምውስተ ተቅዋመ ማሕቶት ክበበ ርዕሳ ወዓብራዊሃ እምውስቴታ ይኩና ኩሉን ፍሕቆ እምአሐዱ ወርቅ ንፁሕ ትገብር መሐቲሃ ስብዓተ ወትሠርዕ ወሐትወ ወያርእዩ እምአሐዱ ገፅ ዘእምድሕሬሃ ወሥርዓታ እምወርቅ ንፁሕ ፍሕቆ ወትገብር ለዝ ኩሉ ንዋያቲሃ መክሊተ ወርቅ ንፁሕ ዘትገብር ዘኩሉ ንዋያ አርእያ አርአይኩከ በደብር፲

<u>በአማርኛ</u>:- መቅረዝንም ከጥሩ ወርቅ አድርግ መቅረዙ ከፅግሩና ከአገዳው በተቀጠቀጠ ሥራ ይደረግ። ጽዋዎቹም ጉብጉቦቹም አበቦቹም አንድነት በርሱ ይደረጉበት በስተጎድኑ ስድስት ቅርንጫፎች ይውጡለት ሦስቱ የመቅረዙ

www.ethiopianorthodox.org

ቅርንጫፎች በአንድ ወገን ሦስቱም የመቅረዙ ቅርንጫፎች በሌላ ወገን ይውጡ ባንደኛውም ቅርንጫፍ ጉብጉብና አበባ ሦስቱም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ፅዋዎች እንዲሁም ከመቅረዙ ለሚመጡ ለስድስቱ ቅርንጫፎች አድርግ በመቅረዙም ጉብጉቦችንና አበቦችን አራት የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ፅዋዎች አድርግ።

ከመቅረዙ ለሚመጡ ለስድስቱ ቅርንጫፎች ከሁለት ቅርንጫፎች በታች አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ ጉብጉብ፣ ከሁለትም ቅርንጫፎች በታች አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ አንድ ጉብጉብ፤ ደግሞ ከሁለት ቅርንጫፎች አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ ጉብጉብ ይሁን ጉብጉቦቹና ቅርንጫፎቹ ሁሉ ከርሱ ጋር አንድ ይሁኑ ሁሉም አንድ ሆኖ ከተቀረፀ ከጥሩ ወርቅ ይደረግ። ሰባቱንም መብራቶች ሥራ። በፊቱ ያበሩ ዘንድ መብራቶቹን ያቀጣጥሉአቸዋል። መኮስተርያዎቹን የኩስታሪ ማድረጊያዎቹንም ከጥሩ ወርቅ አድርግ። መቅረዙም ዕቃውም ሁሉ ካንድ መክሊት ጥሩ ወርቅ ይሠሩ በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ (ዘፀ. 25፣31)

ባሁኑ ዘመን ታቦቱ "ፅላት" እየተባለ ሲጠቀስ ይሰማል። ሰዎች የፅላትንና የታቦትን ልዩነት ሲረዱ አልቻሉም፣ ሊቀነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና አሠርቱ ቃላት የተጻፉበትንና ሌሎችም ፅላቶች ከእግዚአብሄር ተቀብሏል። በግዕዝ ዘይቤ "ፅሌ" ብሎ አንድ፣ ፅላት ብሎ ብዙ ነው በልማዳዊ አነጋገር ግን ነጠላውን ፅላት ይባላል። በብዙ መጻሕፍትም ሠፍሮ ይገኛል የብሉይ ፅላት ማሕደር ወይም ማስቀመጫ ታቦት ይባላል። ፅላት ማለት ትዕዛዛተ እግዚአብሄር የተጻፉበት ሰሌዳ ማለት ነው ታቦት ማለት ደግሞ ማደርያ ማለት ነው።

የሐዲስ ኪዳኑ ፅላት አይደለም ታቦት "ታቦተ እግዚአብሄር፣ታቦተ ምሥዋዕ" ይባላል። ታቦተ ህግ አይባልም። ፅላቷ የምትቀመጥበት የአራት መዓዘን ቅርፅ ያለው ታቦት እንዲሠራ ለሙሴ ከእግዚአብሄር እንደተነገረው በአሪት ዘፀአት ተመዝግቧል። በትዕዛዙ መሠረትም ሙሴ ሠርቷል።

ሙሴ ታቦቱን ከሠራ በኃላ በቅደም ተከተል ሌሎች ንዋየ ቅድሳትንም ሠርቷል። ከንዋየ ቅድሳቱ አንዷ ተቅዋመ ማሕቶት ናት። ተቅዋመ ማሕቶት እጅግ ከተጣራ ንፁሕ ወርቅ ብቻ የተሠራች ናት የሌላ ንጥረ ነገር ቅልቅል የላትም።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለፀው ስለ ተቅዋመ ማሕቶት አሠራር ማንም ሰው በቀላሉ ሊረዳው አይችልም ፤ ከላይ ከሰፈረው የመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ የተቅዋሟ አሠራር እንደሚከተለው ባጭሩ ይገለፃል።

የተቅዋመ ማሕቶት መካከለኛው ክፍል ከታች ወደ ላይ ቀጥ ያለ ዘንግ መሰል ቅርፅ ያለው ነው። እሱም ለውበት ተብለው የተቀረፁ ምልክቶች እሉት ቀጥ ብሎ እንዲቆም ከግርጌው ሰፋ ያለ ጠፍጣፋ አካል አለው። ይህ ዘንግ መሰል አካል ከጫፉ ላይ የአበባ እንቡጥ ወይም የእንቾል ቅርፅ የመብራት ማስቀመጫ አለው። በቀኝ ሦስት፣በግራ ሦስት ተጨማሪ አፅቆች (ቅርንጫፎች) መነሻቸው ከቀጥተኛው ወጥ ዘንግ መሰል ቁስ ከወደ ላይ ሆኖ በሦስት የተከፈለ ነው ከጫፉ ላይ ግን አፅቆቹም (ቅርንጫፎቹም) ሆኑ መካከለኛው ዘንግ እኩል ናቸው። የሁሉም አፅቅ (ቅርንጫፍ) ቁጥር ሰባት ይሆናል። በግዕዝ መሣውር ይባላሉ ግዕዙን ብሉይ ኪዳን ወደ አማርኛ የመለሱ ምሑራን "ጉብጉቦች" ብለዋቸዋል። ጉብጉቦቹ እያንዳንዳቸው በተለያዩ ቅርፆች የተዋቡ ናቸው። ከጫፋቸው ላይ የለውዝ የአበባ ጉንጉንና ሌሎችም የጌጥ ዓይነቶች ተደርገውላቸዋል። ለውበት የተለያዩ ቅርጾች ቢደረጉላትም ከንፁሕ ወርቅ በቀር ሌላ ንጥረ ነገር አልተቀላቀለባትም (ተቅዋሟ) ከንፁሕ ወርቅ የተሠራችበትን ምክንያት ትርጉም የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በየዘመናቸው ገልፀውታል። የነሱ አገላለፅ በሰፊው ወደፊት ይገለፃል።

ዘመነ መሳፍንት እስኪፈፀም ድረስ ተቅዋመ ማሕቶት በደብተራ ኦሪት የመንፈሳዊ አገልግሎት ንዋየ ቅድሳት ሆና ቆይታለች። የዕብራውያን የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል ሲሆን ዳዊትና ሰለሞን ከሱ ቀጥለው በቅደም ተከተል ነግሠዋል። ቤተ መቅደስ በሰለሞን ተሠራ። ከሳኦል እስከ ሴዴቅያስ 23 ነገሥታት በዕብራውያን ላይ እንደ ነገሱ ጊዮርጊስ ወልደአሚድ ያስረዳል 23ኛው የእስራኤል ንጉሥ ሴዴቅያስ ሁለት ስም አለው። የመጀመርያው ስሙ ምናሴ ሲሆን 2ኛው ሴዴቅያስ ነው። " ሴዴቅያስ "ብሎ የሰየመው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ነው። (በጊዮርጊስ ወልደ አሚድ አገላለፅ)



www.ethiopianorthodox.org 

በሦያ ሦስቱ የዕብራውያን ነገሥታት ዘመን ተቅዋመ ማሕቶት የቤተ መቅደስ መገልገያ በመሆን ቆይታለች። ከመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 36፣1 አስከመጨረሻው እንደተመዘገበው የከለዳውያን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወረረ ቤተመቅደስን አቃጠለ የቤተመቀደስንም ንዋያተ ቅድሳት ዘረፈ። ከዕልቂቱ የተረፉትን ዕብራውያን ወደ ባቢሎን ወስዶ በባርነት እንዲገዙ አደረገ። የዕብራውያኑ ባርነት ለ70 ዓመት ቀጠለ።

ከዚያ በኃላ የተቅዋመ ማሕቶት ታሪክ በብሉይ ኪዳን አልተመዘገበም የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶር እስከነገሠ ድረስ ከቤተመቅደስ የተወሰዱ ንዋየቅድሳት በክብር ተጠብቀው ቆይቷል። የሚዲ ንጉሥ ዳርዮስ ብልጣሶርን ሊወጋው ሲንቀሳቀስ ብልጣሶር ወታደሮቹን ልኮ ደመሰሰው። በድል አድራጊነቱ ስለተደሰተ ታላቅ ግብዣ አደረገ በትንቢተ ዳንኤል የተመዘገበው ለ፪ መኳንንቱ ታላቅ ግብዣ ማድረጉን ብቻ እንጂ ግብዣው የተደረገበትን ምክንያት አልተገለፀም ታሪኩን በዝርዝር አስቀምጦት የሚገኘው ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ነው።

በክብር የተቀመጡትን ንዋየቅድሳት ብልጣሶር ለዕቁባቶቹና ለመኳንንቱ መጠጫ አደረጋቸው ይህን በማድረጉ ከንጉሥነቱ ተገለበጠ በጊዮርጊስ ወልደአሚድ አመዘጋገብ ድርጊቱ በ4985 ዓመተ ዓለም ነው የተፈፀመው።

ከኢየሩሳሌም ጥፋት ጀምሮ ስለተቅዋመ ማሕቶት ሁናቴ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሌላ ታሪክ የተገለፀ ነገር የለም ዕብራውያን በየዘመናቱ የተፈፀሙትን ታሪኮቻቸውን የሚመዘግቡበት ልዩ ማሕደር ነበራቸው ይህ ማህደር "ታልሙድ" በመባል ይታወቃል። ዕብራውያን የታቦተ ጽዮንን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የማይቀበሉት ታሪኩ በታልሙድ ስላልተመዘገበ ነው።

ሰባ ዓመት የዕብራውያንን የስደት ዘመን ሲፈፅም ዕብራውያን ወደሐገራቸው ተመለሱ በነሱም የቤተመቅደስ ዕድሳት ሥራ ተካሄደ በሰሎሞን የተሠራውን ያህል ባይሆንም ቤተመቅደሱ ታድሷል። የቤተመቅደሱ የዕድሳት በዓል እስከ ዘመነ ሐዲስ በየዓመቱ ይከበር ነበር ( ዮሐ .10፣22)

የቤተመቅደሱን ዕድሳት ለማካሄድ ቁፈራ ሲደረግ ተቅዋመ ማሕቶት በፍርስራሹ ውስጥ ተቀብራ እንደተገኘች የብሉይ ኪዳን የአርኪኦሎጂ ምሁራን ይናገራሉ። የመገኘቷም ታሪክ በታልሙድ እንደተመዘገበ አልፎ አልፎ ይነገራል። ሌሎቹ ንዋየቅድሳት በሙሉ ጠፍተው ተቅዋመ ማሕቶት ብቻ ስለተገኘች ልዩ እንክብካቤ ይደረግላት ነበር ከጥንት ያልነበሩትን ሁለት ቅርንጫፎች በትቅዋሟ ላይ ተጨምረው የቅርንጫፎቹ ብዛት ዘጠኝ ሆኗል።

ቤተመቅደስ በዘሩባቤል ዘመነ መንግሥት ከታደሰ በኃላ ለአምስት መቶ ዓመታት ያህል የሌላ ጊዜ ዕድሳት ሳይደረግለት ስለኖረ በዘመነ አራቱ መጨረሻ ገደማ በጣም አርጅቶ ይታይ ነበር። ከዚሀ ጊዜ ጀምሮ ሄሮድስ የቤተመቅደሱን እድሳት በሰፊው ተያያዘው። የእድሳቱ ዘመን ከ20 እስከ 30 ዓመት እንደወሰደ ይነገራል ሄሮድስ ከ40፪ በላይ የናዝሬትንና የገሊላን ሕፃናት በግፍ በመፍጀቱ ወደር የማይገኝለት አረመኔ ሆኖ እያለ ቤተመቅደስን በመሥራቱ ትልቁ እየተባለ ይጠቀሳል።

ይህ ቤተመቅደስ በ70 ዓመተምሕረት ጥጦስ የተባለው ሮማዊ እንዳልነበረ አድርጎ አጥፍቶታል። ተቅዋመ ማሕቶት ከዚሀ ጊዜ ጀምሮ የት እንደደረሰች አልታወቀችም እንደ አንዳንድ የታሪክ ምሑራን በሮማውያን ተወስዳለች ሲሉ ሌሎች ደግሞ ከሞት የተረፉት ዕብራውያን ይዘዋት ተሰደዋል ከዚያውም በአሕዛብ እጅ ወድቃ ይሆናል ይላሉ።

የዳዊት ከተማ ኢየሩሳሌም ከባቢሎን ምርኮ ጀምሮ ከአራት ጊዜ ያላነሰ ወረራ ተፈፅሞባታል። ከዚህም የተነሳ በተለያዩ የዓለም የከርሰ ምድር ምርምር ሊቃውንት (አርኪኦሎጂስቶች) ጥረት ለብዙ ዘመናት ተቀብረው የኖሩና የብሉይ ኪዳንም ሆነ የሐዲስ ኪዳን ምንነትን የሚያሳዩ ቅርሶች ሊያገኙ ችለዋል። በምድር ገፅ የሚታይ ቅርስ ግን በኢየሩሳሌምም ይሁን በአካባቢዋ አንድም ለምልክት አልተገኘም። የኢትዮጵያውያን ዳግማዊት ኢየሩሳሌም በሆነችው አክሱም ከተማና አካባቢዋ ከኢየሩሳሌም ባልተናነሰ ሁኔታ ጥፋት ተፈፅሟል። የ10ኛውና የ16ኛው ክፍለ ዘመናት በዚችው ከተማ የተፈፀመው አረመናዊ ጥፋቶች በዋነኝነት ይጠቀሳሉ።

ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ግን አክሱም እንደ እየሩሳሌም [illegible]ብረው የወደቁም ሆነ ምንነታቸው

www.ethiopianorthodox.org

ሳይነካ እንደቆመ የሚገኙ ብዙ የድንጋይ ሐውልት ማስረጃዎች በአክሱም ከተማ ይገኛሉ ያ ሁሉ የዋፋት ዘመን አልፈው ለዚህ ትውልድ መተላለፋቸው ምሥጢር ለሰብአዊ አእምሮ እጅግ ረቂቅ ነው እንኳንስ የቆሙ ሐውልቶች የወደቁትና የተሠባበሩትም በላያቸው ላይ የሠፈረውን ማስረጃ እንደያዙ ነው የሚገኙት።

በጥንታዊው የአክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን ቅፅር ጥንታዊ ግንብና በቤተክርስቲያኑ የመውጫ ደረጃ ለግንብ ሥራ ውለውና በክብር ተጠብቀው የሚገኙ ብዙ ጥንታዊያን የትልቁ ሐውልት ተመሳሳይነት መልክ ያላቸው ይታያሉ። በነዚህ ቅርሶች የተለያዩ ጽሑፎች በግርክኛ፣በሳባና በግዕዝ ቋንቋዎች የተጻፉ መመልከት አክሱምን ለሚጎበኝ ሁሉ የተለመደ ነው። እነዚህ ጥንታውያን የድንጋይ ቅርሶች የተጀከመውት ታሪካዊ ማስረጃ በጽሑፍ ብቻ የተወሰነ አይደለም የብሉይንና የሐዲስን ንዋያተ ቅድሳትም በቅርፅ ተሥለውባቸው ይገኛሉ። በነሱ ላይ ተቀርፀው ከሚገኙት የብሉይ ኪዳን ንዋያተ ቅድሳት መካከል የተቅዋመ ማሕቶት ቅርፅ ይገኛል ተቅዋመ ማሕቶት በቤተክርስቲያኑ ቅፅር ግቢ (በጥንታዊው የአክሱም ቤተክርስቲያን) ተቀርፃ የምትገኝባቸው ትናንሽና ትላልቅ ድንጋዮች ብዙ ናቸው። ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ቅርፅ እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ መንፈሳዊ ስሜትን የሚቀሰቅስ ነው። ይህን አስደናቂ ግሩም ታሪክ ጠብቀው ላሁኑ ትውልድ ያቆዩ ጥንታውያን የአክሱም ከተማ ነዋሪዎች አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል።

## ዘካርያስ ርእየ ተቅዋመ ማሕቶት (ዘካርያስ ተቅዋመ ማሕቶትን አየ)

የተቅዋመ ማሕቶት ታሪክ ከማንም ቤተክርስቲያን በበለጠ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጎልቶ ይታወቃል። የሕዳር ጽዮን መንፈሳዊ በዓል ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙና በእመቤታችን ስም በተመሠረቱ ታላላቅ አድባራትና ገዳማት እጅግ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል። በአክሱም ጽዮንና በአዲስ ዓለም ማርያም ደብር በየዓመቱ የሚታየው የመንፈሳዊ ክብረ በዓል ሥነሥርዓት በጥንኛንነት ሊጠቀስ ይችላል። የ... በዓል በኢትዮጵያ መከበር የጀመረበት ዘመን መቼ እንደሆነ ለመናገር አልተቻለም ወደፊት ተጠንቶ ሊገለፅ ይችላል። ለመከበሩ ግን በቂ ምክንያት አለው።

ለበዓሉ መከበር ዋና መሠረት የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በቅድሚያ እንመለከታለን ግዕዝ "ርኢኩ ተቅዋመ ማሕቶት ዘኩለንታሃ ወርቅ ወማሕቶት ዲቤሃ ወሰብዓቱ መሐትው በላዕሌሃ ወስብዓቱ መሣውር በዘይሰቅይዎን ለመሐቲዊሃ ዘዲቤሃ"

አማርኛ እነሆ ሁለንተናውን ወርቅ የሆነውን መቅረዝ አየሁ የዘይትም ማሰሮ በራሱ ላይ ነበረ። ሰባትም መብራቶች ነበሩት በራሱም ላይ ለነበሩት መብራቶች ሰባት ቧንቧዎች ነበሩዋቸው (ትንቢተ ዘካርያስ 4፣2-4)

የእግዚአብሔር ቃል ለአራት መቶ ዓመት ያህል ከሰዎች ርቆ ነበር። ማለትም ከሙሴ ጀምሮ እግዚአብሄር ለዕብራውያን ከመካከላቸው ነቢይን እያስነሳ ያስተምራቸው ይመክራቸውና ይገሥፃቸው ነበር። ከዘመነ ዘካርያስ በፊት ካለው ዘመን ጀምሮ ራሱ ዘካርያስ እስከተነሳበት ድረስ ለአራት መቶ ዓመታት ከዕብራውያን አንድም ነቢይ እንዳልተነሳ የብሉይ ኪዳን መምህራን ያስረዳሉ።

ዘካርያስ በሚል ስም ከሃያ በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል። ከነዚህም መካከል የሁለት የዚህ ስም ተጠሪዎች ታሪክ ከዚህ ላይ እንመለከታለን ከትንቢተ ሐጌ ቀጥሎ ያለውን የትንቢት መጽሐፍ የጻፈ ነቢይ ዘካርያስ ይባላል። የግዕዙ ብሉይ ኪዳን የዚህ ነቢይ አባት በራክዩ፣እያቱ አዶ እንደሆነ ይገልጻል "ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ ዘካርያስ ወልደበራክዩ ወልደ አዶ" ሲል አማርኛው ግን አባቱ አዶ አያቱን በራክዩ ያደርገዋል። ሁለተኛው ዘካርያስ የመጥምቁ዗ ዮሐንስ አባት ነው። የዚህም አባት በራኪዩ ይባላል መሥከረም 8ና የካቲት 15 የሚነበቡ የሥንክሣር ምንባቦች ሁለቱንም ከደቂቀ ነቢያት ቁጥር ያስቀምጣቸዋል። ስለ መጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ በሥንክሣር የተመዘገበው ቅዱስ፣ስግዕትና ካሣን የሚሉትን ቅጽሎች ያስቀምጣል። ነቢይ አላለውም የሰቱን ቅጽሎች (ክህነት፣ነቢይና ስግዕት) በመደጋገም ዘካርያስ ለሚለው ስም

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ ሠጥቶት ይገኛል በሌላ ቦታ ሦስቱ ተደራርበው ዘካርያስ ለሚለው ስም እምብዛም ተቀጽለው አይገኙም። የአዶ ልጅ ዘካርያስ በተፈጥሮ በሽታ መሞቱን ሥንክሣሩ(የየካቲት 15) ያስረዳል። የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ በሰማዕትነት እንደሆነ የሞተው ከሐዲስ ኪዳን (ማቴዎስ 23:35)ጀምሮ የተለያዩ የቤተክርስቲያን መዛግብት ይገልጻሉ። የቤተክርስቲያን መምህራን በሁለቱ ስሞች እንደተለያዩ ይኖራሉ። አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ በተረጎሙት ትንቢተ ሕዝቅኤል ካህን፣ነቢይና ሰማዕት የተባለው የአዶ ልጅ ዘካርያስ እንደሆነ መገለፁ ይነገራል። ሌሎች ደግሞ ነቢይ፣ካህንና ሰማዕት የተባለው የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ መሆኑን ይናገራሉ። ይህን አባባል የማይቀበሉ ክፍሎች በበኩላቸው መክራ የተቀበሉትን ነቢያት ሰማዕትነትን ተቀብለዋል(ወኲሎሙ ሰማዕተ ካኑ በሃይማኖት) (ዕብራ.39:40) ስለሚል የአዶ ልጅ ዘካርያስ ሰማዕት ተባለ ወደማለት ይቃጣቸዋል። በሁለቱ ስሞች እስካሁን ከስምምነት አልተደረሰም። ቅዱስ ያሬድ ዘካርያስ ከሚለው ስም ተነስቶ ሦስቱን ቅጽሎች (ካህን፣ነቢይና ሰማዕት) ስለሚያስቀምጥና የታሪክ መጻሕፍት የአዶ ልጅ ዘካርያስ በተፈጥሮ ሕመም መሞቱን ስለመዘገቡ መለያየቱን ያጎላዋል ቅዱስ ያሬድ ዘካርያስን ሊቀካህናትም ይለዋል። ዘመናውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎች በማቴዎስ ወንጌል 23:35ና በሉቃስ 11:51 የተመዘገቡትን መሠረት በማድረግ አንድ የድሮ ፀሐፊ በአባት ስም ተሳስቶ ይሆናል የማለት አጠቃላይ አስተያየት አላቸው። (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገፅ 201)

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለአራት መቶ ዓመት ያህል ቃለ እግዚአብሄር ከሰው ልጆች ተለይቶ ከቆየ በኋላ ወደ ዘካርያስ መጣ ( ወአመተስዑ ለጽልመት ዘዐሠርቱ ወአሐዱ ወርኅ በወርሐሳባጥ ኮነ ቃለ እግዚአብሄር ኀበ ዘካርያስ ወልደበራክዩ በዳርዮስ በሁለተኛው ዓመት ሳባጥ በሚባል በ11ኛው ወር በ24ኛው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ ወደ ዘካርያስ መጣ ትንቢተ ዘካርያስ 1፣7– 8)

በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር ሳባጥ የወርሐ የካቲት ስም ነው። ይህ ወር ለነሱ አሥራ አንደኛው ነው ምክንያቱም የዕብራውያን የዓመት መጀመሪያ ሚያዝያ ነውና። ይህም የሆነበት ከግብፅ ባርነት በዚሁ ወር ስለወጡ ነው። ይህን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት" ዘካርያስ ርእየ ለወርኃሳባጥ በሰርቁ ተአምረኪ ዘዘይት ማዕከለ ክልኤ አእፁቅ፤ ማርያም ጽዮን ለብርሃን ተቅዋመ ወርቁ፣ ዕዝራኒ በገዳም አመወአለ ውዳቁ ለሕብረገፅኪ ፅጌ ሐተወ መብረቁ" የሚለውን ድርሰት አዘጋጅተዋል።

በአራት ዘፀአት 25፣31 ስለ ተቅዋመ ማሕቶት የተመዘገበውን መሠረት ያደረገ ራዕይ ለዘካርያስ ታየ ራዕዩን ያየበት ወርም የካቲት መሆኑን በቅዱስ መጽሐፍ የተደገፈ ማስረጃ እንዳለው ከላይ ተገልጿል። ዘካርያስ ያየው ራእይ በተቅዋመ ማሕቶት አማካኝነት ስለ እመቤታችንና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን መወለድ ነው። በራዕይ ያየው ይህንንም በየዘመኑ የተነሱ የዘመነ ሐዲስ ሊቃውንት አመስጥረውና አብራርተው አስቀምጠውታል። ቅዱስ ኤፍሬምና ቅዱስ ያሬድ በዚሁ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዘው ይገኛሉ። የሁለቱን ሊቃውንት ስለ ተቅዋመ ማሕቶት በየራሳቸው ከዚህ ቀጥሎ ይታያል።

ሀ. <u>ተቅዋመ ማሕቶት በቅዱስ ኤፍሬም ፦</u> ቅዱስ ኤፍሬም በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ የነበረ የሶርያ ተወላጅ ነው። የቅዱስ ያዕቆብ ዘንፅቢን ተማሪ ነበር። መምህሩን ተከትሎ በኒቅያ ጉባዔ ተከፍሏል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከተረጎሙና በዚሁም ብዙ መጻሕፍትን ከጻፉ ሊቃውንት ቅዱስ ኤፍሬም አንዱ ነው። ቅዱስ ኤፍሬም የቤተክርስቲያን ዜማንም አዘጋጅቷል የሱ ዜማ ግን እንደ ቅዱስ ያሬድ ዜማ ተጠብቆ አልኖረም ጠፍቷል።

ከቅዱስ ኤፍሬም ድርሰቶች ውስጥ ውዳሴ ማርያም ብቻ በኢትዮጵያ ይገኛል።
ስለ እመቤታችን ውዳሴ የተጻፉ መጻሕፍት ሁሉ በውጭ ቋንቋ "ማርዮሎጊ" በመባል ይታወቃሉ "ነገረ ማርያም" የሚለው ስያሜ ይህን ሊወክል እንደሚችል አንዳንድ የኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያን ምሑራን ይናገራሉ። ይሁን እንጂ "ነገረ ማርያም" የሚለው ስያሜ ስለ እመቤታችን የተጻፉትን በሙሉ ሊተካ አይችልም። ነገረ ማርያም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስለ ስደት የተጻፈ መጽሐፍ መጠርያ ነው። ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ድርሰቱም ም.7 ቁ.5 ላይ የሚከተለውን ስለ ተቋም ትርጉም ጽፏል " አንቲ ውእቱ ተቅዋም ዘወርቅ እንተ ያርኢ ማሕቶተ ፀዳል ኩሎ ጊዜ ዘውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ብርሃን ዘእምብርሃን ዘአልቦ ጥንት አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ ወለምፅአቱ አብርሃ ላእሌነ ለእለንነብር ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ወአርትአ ዕገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም በምሥጢረ ጥበቡ ቅዱስ"

<u>አማርኛው</u>:-ሀ. "ብርሃንነት ያለውን ፋና የተሸከምሽ የወርቅ ተቅዋም አንቺ ነሽ ለዓለም ብርሃን የሆነ ጥንት ከሌለው ብርሃን የተገኘ ብርሃን ከአምላክ የተገኘ አምላክ ሳይለወጥ ካንቺ ሰው የሆነ ሰውም በመሆኑ በጨለማ ለምንኖር ለኛ አበራልን እግሮቻችንም ወደ ሰላም አቀናልን። "

በዚህ ምንባብ ተቅዋም (መቅረዝ) የተባለችው ቅድስት ድንግል ማርያም መሆንዋን እና ማሕቶት የተባለውም ጌታችን መሆኑን በግልጽ ቅዱስ ኤፍሬም አስቀምጦታል ሌሎቹ ከዚሁ ጋር የተዘረዘሩት የወልደ እግዚአብሔር የማዳን ሥራዎች ናቸው።

### ለ . <u>ተቅዋመ ማሕቶት በቅዱስ ያሬድ</u>:-

በቅዱስ ያሬድና በቅዱስ ኤፍሬም መካከል የሁለት መቶ ዓመት ያህል ልዩነት አለ። ቅዱስ ኤፍሬም በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበረ ሲሆን ቅዱስ ያሬድ ሁለት መቶ ዓመት ቆይቶ በስድስተኛው ክፍለ ዘመን የተነሳ ነው። የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ብዙ ቁምነገሮችን ያስገነዝበናል። የቤተክርስቲያን ዜማ ከቅዱስ ያሬድ ቅርሶች ትልቁና ዋነኛው ሲሆን የጥንቱን የኢትዮጵያውያን የቅዱሳት መፃሕፍት ትረጉም ጥንታዊ ስነፅሁፍ ጥንታዊ ታሪክ ጥንታዊ የኢትዮጵያውያን መነኮሳት ገዳማዊ ሕይወትና ሌሎቹም ከሱ ድርሰት ነው የሚንፀባረቁት ተቅዋመ ማሕቶት በቅዱስ ያሬድ ከተተረጎሙት ወይም በዘመኑ ከነበረው የሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አተረጓጎም በያሬድ ዜማ ከሚገኙት አንዷ ናት። ቅዱስ ያሬድ ተቅዋምን ለእመቤታችን ማሕቶትን ለጌታ እየሰጠ በበዓላተ እግዝእትነ ማርያም ለምሥጋና ከሚቀርቡት መዝሙሮቹ አቅርቧል። በምዕራፍ፣በዝማሬ መዋሥዕትና በድጓ የተቅዋመ ማሕቶትን አመሥጥሮ ያልገለፀበት ክፍል የለም። ከተጠቀሱት ድርሰቶቹ በተጨማሪ "አንቀፀ ብርሃን" በመባል የሚታወቅ የፀሎት መጽሐፍ አለው ። በዚሁ መጽሐፍ በ8ኛው ምዕራፍ ተቅዋም ከሚለው ቃል ተነስቶ ስለ ምስጢረ ሥጋዌ ሠፊ ትምህርት ሠጥቷል።

የትምህርቱ ምንባብ ከዚህ በታች ቀርቧል "አንቲ ውእቱ ተቅዋም ዘወርቅ ዘኢገብራ እደኬንያ ዘሰብእ ወኢየሐትው ውስቴታ ማሕቶተ እሳ ለሊሁ ብርሃን እብ ብርሃን ዘእምብርሃን መጽአ ኀቤኪ መንበረ መለእልቴኪ ወአብርሃ በመለኮቱ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም፣ሰደደ ጽልመተ እምላእለሰብእ ወአድሐነነ በቃሉ ማሕየዊ እንዘይብል አነውእቱ ብርሀኑ ለዓለም እመኑ በብርሃኑ ወእንዣሥሙ እንዘብክሙ ብርሃን"

<u>አማርኛ</u>:- የብልሐተኛ እጅ ያልሠራት በውስጧም መብራት የሚያበሩባት የወርቅ መቅረዝ አንቺ ነሽ ራሱ የአብ ብርሃን ያበራባታል እንጂ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ወዳንቺ መጥቶ አደረ በመለኮቱም በዓለም ሁሉ አበራ ጨለማን ከሰዎች ላይ አራቀ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ " <u>በኔ</u> <u>በብርሃን እመኑ</u> ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ ብሎ በሚያድን ቃሉ አዳነን"

የብሉይ ኪዳንዋ ተቅዋም በሙሴ እጅ እንደተሠራች ብሉይ ኪዳን ያስረዳል። የሠራትም በእግዚአብሄር እየተመራ ነው። በሙሴ ተቅዋም ዘወርቅ(ተቅዋመ ወርቅ) ስትባል በትንቢተ ዘካርያስ ተቅዋመ ማሕቶት ትባላለች። ቅዱስ ያሬድ ተቅዋም ዘወርቅ(ተቅዋመ ወርቅ) የሚለውን ሀረግና ተቅዋመ ማሕቶት የሚለውን ሀረግ በተለያዩ ድርሰቶቹ አስገብቷቸዋል። "ተቅዋም" የምትለውን ቃል ለብቻዋ ያስቀመጠበት የምሥጋና መዝሙርም አልፎ አልፎ እናገኛለን ለማስረጃም ያህል

"ተቅዋምኑ ንብለኪ ማሕቶተ ብርሃን ወልድኪ ሐዋርያቲሁ መሣውርኪ ላእካነ ምሥጢሩ ለበኩርኪ"

<u>አማርኛው</u>:- "ተቅዋም እንልሻለን ልጅሽ የብርሃን ፋና ነው። የሱሐዋርያት ቅርንጫፎችሽ የልጅሽ ምሥጢር መልእክተኞች ናቸው። የሚል የምሥጋና መዝሙር እናገኛለን፤ ቅዱስ ያሬድ "ተቅዋመ ማሕቶት ተቅዋመ ወርቅ፣ተቅዋም" እያለ የገለፃቸው መዝሙሮች እጅግ ብዙ ናቸው።

ከዚህ በላይ ከተነገረው ምንባብ እመቤታችንን "ተቅዋም እንልሻለን" ካለ በኋላ መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በብርሃን ፋና ሐዋርያትን በተቅዋምዋ አፅቆች (ቅርንጫፎች) በመመሰል አስቀምጦአቸዋል።

ተቅዋመ ማሕቶት የሚለው ሐረግ ሲነገር ማሕቶት ለጌታ ተቅዋም ለእመቤታችን ምሳሌ ይሰጣሉ። ተቅዋመ ማሕቶት በድጓ ውስጥ ይልቁንም በህዳር ጽዮን መንፈሳዊ ክብረ በዓል ላይ በሚዘመረው ምሥጋና በሰፊው ተዘርዝሯል። እያንዳንዱን ከዚህ ላይ መዘርዘር ግን አላስፈለገም።

ነቢያት ከመንፈስ ቅዱስ በተሠጣቸው ሐብተ ትንቢትና ሐብተ ትምህርት ያለምንም ፍርሐት በየዘመናቸው አስተምረዋል ሐዋርያትም ከአምላካቸውና ከመምህራቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሠጣቸው መመሪያ ከምድረ ፍልሥጥኤም ውጭ ብዙ አህዛብን ስላስተማሩ ብርሃናተ ዓለም (የዓለም ብርሃናት) ተብለዋል። ቅዱስ ያሬድ ሐዋርያትን የተቅዋም ጉብጉቦች (መሣውር) አላቸው። በአራት ዘፀአት በመነሳት ነቢዩ ዘካርያስ ስለተቅዋመ ማሕቶት በመንፈስ ትንቢት ,ያየውና ሁለቱን የአራት ዘፀአቱንና የትንቢተ ዘካርያስን ምሥጢር የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት እንዴት እንደተረጎሙት ባጭሩ ለመግለፅ ተሞክሯል።



# <u>ምዕራፍ 2.</u>

## <u>ጽዮን</u>

ጽዮን የቦታ ስም ነው። ከአርሞንኤም ተራራ በስተግርጌ የሚገኝ ቦታ እንደሆነ በብሉይ ኪዳን ተገልጿል (መዝሙረ ዳዊት 132፣3) በዚሁ ቦታ ብዙ ኮረብታዎች ይገኛሉ ኮረብታዎቹ ትናንሾቹ ተራራዎች አድባረ ፅዮን በመባል ይታወቃሉ ከረጅሙ ተራራ ከአርሞንኤምም ጫፍ ላይ በረዶ አይለይም በረዶው እየሟሟ (እየቀለጠ) ውሃው ወደ አድባረ ጽዮን ይፈሳል። ይህ ውሃ የበረዶ ውሃ በመሆኑ እጅግ ንፁሕ ነው። ነቢዩ ዳዊት የሰው ልጆች በወንድማማችነት ከአርሞንኤም ወደ ፅዮን ተራራዎች እንደሚወርድ ንፁሕ ውሃ ያለ ንፁሕ ፍቅር ኑሮአቸው በስምምነት ቢኖሩ ምንኛ መልካም ነው አለ።

በሰለሞን የተሠራው የመጀመሪያው ቤተመቅደስ ከፅዮን ኮረብታዎች ባንዱ ነበር ፅዮን የሚለው ቦታ የሚገኘው ኢየሩሳሌም ውስጥ ነው። በአጠቃላይ ፅዮን ማለት ኢየሩሳሌም ነው ። ኢየሩሳሌም ማለትም ፅዮን ነው። ከቦታው መነሻነት እግዚአብሄር ጽዮንን ማደርያው ትሆነው ዘንድ መረጣት ብሏል። (መዝ.131፣13) ምሥጢራዊ ትንቢቱ ግን ለእመቤታችን የተነገረ ነው። ሊቀ ነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና ከእግዚአብሄር ፅላት ተቀብሏል።

ፅላቷ የምትቀመጥበት ባለመከደኛ ታቦት እንዲሠራም ከእግዚአብሄር ተነግሮታል። በግዕዝ ሰዋሰው ፅላት ለብዙ ነው ነገር ግን በዚሁ ስለተለመደ እንዳለ ተፅፏል። ታቦት ማለት ማደርያ ማለት እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል።

ጽዮን ከሚለው ቃል በመነሳት የሚሠጠው ምሥጢራዊ ትርጉም እጅግ ብዙ ነው። በብሉይ ኪዳን ይህ ቃል ያልሠፈረበት ቦታ የለም መምህራን ቤተክርስቲያን በየዘመኑ ይህን ቃል ተርጉመውታል። ምሳሌነቱ ለቤተክርስቲያንና ለእመቤታችን ነው የሰጡት። ኢየሩሳሌም ሰማያዊትና ኢየሩሳሌም ምድራዊት በመባል ለቤተክርስቲያን በምሳሌነት ይተረጎማል "ይባርክ እግዚአብሄር እምፅዮን" የሚለው የግዕዙ

www.ethiopianorthodox.org

መዝሙረ ዳዊት ምንባብ በአማርኛ ጽዮን ሰማያዊት ጽዮን ምድራዊት ብለው ተርጉመውታል። አባባሉ ለቤተክርስቲያን ብቻ የተሠጠ ነው። ቤተክርስቲያን በዓፀደ ነፍስና በዓፀደ ሥጋ ትገኛለች። የማሕበረ መላእክትና የማሕበረ ክርስቲያን አንድነት ናት። " ተንሥዕ እግዚኦ ወተሰሃለ ለጽዮን (መዝ. 101፤13) "የሚለው ምንባብ በአማርኛ አቤቱ ኢየሩሳሌምን ይቅር በላት ተብሏል ይህን አረፍተ ነገር ተርጓሚዎች ሰፊ ገለፃ ሠጥተውበታል። የባቢሎውያን ኢየሩሳሌምን መውረር አስመልክተው ነው ገለፃውን ያሠፈሩት ከዚህ ስለ እመቤታችንም ሆነ ስለ ቤተክርስቲያንም ምንም ያሉት የለም።

የአንድምታው ትርጉም ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ተጀመረ። ከዚያ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ግዕዝ በግዕዝ ሆኖ የብሉይና የሐዲሱ የአተረጓጎም መንገድ የተለያየ ነበር። የብሉዩ መንገድ "ይቤ መተርጉም" እየተባለ ሲነገር የሐዲሱ ደግሞ "ድሕረ ወንጌል" የሚል መንገድ ነበረው። ከዚህ በተረፈ በቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች የብሉዩ፣ የሐዲሱና የሊቃውንቱ ጥንታዊ ትርጉም ለማግኘት ይቻላል። ቤተእሥራኤል፣ ቤተክርስቲያንና ገበዝ አክሱም የሚሉ ሐረጎች ከጥንታዊው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም በተያየዙ ምሥጢራዊ አመጣጥ አላቸው። ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ወገናዊነትን፣ ዜግነትን የሰው ልጅ በጥምቀት ሐብተውልድናን (ፀጋ መንፈስ ቅዱስን) መቀበሉን ያሳያል። ተቅዋምና ጽዮን በሁለት ቃላት ተከፍለው የየራሳቸውን ታሪካዊ አመጣጥና ትርጉም ለመግለጽ እስካሁን የተለያዩ ማስረጃዎችን መዘርዘር ተችሏል። የመጽሐፉ (የዚህ መጽሐፍ) ርእስ ተቅዋመ ጽዮን ነው። የሁለቱን ቃላት (ተቅዋምና ጽዮን) ዝርዝር ሁናቴ ከተገለፀ በኃላ ሁለቱን ቃላት አገጣጥሞ ባንድ ሐረግ በማስቀመጥ ሐረጉ የመጽሐፉ ርእስ እንዲሆን የተመረጠበት ዋና ምክንያት ሁለቱም (ተቅዋምና ጽዮን) ከምሥጢረ ሥጋዌ ጋር የተያያዘ ሰፊ የቤተክርስቲያን ትምህርት ስላላቸው ነው። ተቅዋመ ጽዮን ለወደፊት በሰፊው ተዘርዝሮ ሊወጣ ይችላል። ማንም መጽሐፍ በቅድሚያ ባጭሩ ከወጣ አንባቢያን ፍሬ ነገሩን በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ እንደ መግቢያ ይሀንላቸዋል። በተቅዋመ ጽዮን አገላለጽ ሌላ ሐሳብ ተከስቶላቸዋል ወደ ቅዱስ መጽሐፍ ገባ ብለው ከዚህ በተሻለ መልኩ ሊያዘጋጁ የሚችሉ ሰዎች ለኖሩ እንደሚችሉ ተስፋ ያደርጋል።

## ቅኔና ሂደቱ

ይህ ቃል ቀነየ ከሚለው ከግዕዝ ግሥ አወራረድ የሚወጣ ጥሬ ዘር ነው። ስለሆነም ቃሉ በአማርኛና በትግርኛ ቋንቋዎች ተዘውትሮ ሲነገር ይገኛል። በጋጣሚነታቸው የታወቁት የጥንትና የዘመናችን ደራሲያን "ባለ ቅኔዎች" እየተባሉ በአማርኛ ቋንቋ ይጠቀሳሉ ቃሉ እጅግ ጎልቶ የሚነገርላቸው የጥንታዊት ግሪክ ፈላስፋዎች ናቸው። በተለይ ሆሜር በዚሁ አጠራር ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል።

የግዕዝ ቋንቋ ሴማዊ ስለሆነ በብዙ ቃላት ከዕብራይስጢ ከሱርስትና ከዐረብኛ ቋንቋዎች ጋር ይገናኛል በተለይ በግሥ አወራረድ መንገድ ከእብራይስጢ ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አለው ስለዚህ በግዕዝ በትግርኛና በአማርኛ ቅኔ እየተባለ የሚጠቀሰው ቃል በእብራይስጢ "ቆኔን" እንደሚባል የዕብራይስጢ ቋንቋ ምሑራን ሲያስረዱ በዚሁ ለብዙ ትርጉም እንደሚውል ያረጋግጣሉ። ሙሆ ማልቀስ መቆዘም መዝፈን መግጠም ማጉረምረምና ማቀንቀን ለማለት የዕብራይስጢ ቋንቋ ተናጋሪዎች "ቆኔን" የሚለውን ቃል ብቻ እንደሚጠቀሙ ከምሑራኑ ዘገባ እንረዳለን።

ቅኔና ቃና "ቀነየ" ከሚለው ግሥ በዘርነት ሊወጡ ይችላሉ ቃና የሚለው ቃል ጣዕመ ዜማን የዜማ ድምፅ የዜማ ሥልት ለማለት ሲያገለግል የቦታ ስምም ይሆናል /2/

ቀንዪ ቀንዮት /ቀንዮ ቀንዮት/ የሚለውን የግሡ ንውስ አንቀፅ በዋጋ ገዝቶ ገንዘብ ማድረግ መግዛት መውሰድ ማለትን ያመለክታል። "... ወውእቱ ይቀንይኪ /3/ የሚለውን ገፅ ንባብ ስንመለከት አንዱ የበላይ ሆኖ በሥልጣን ሌላውን የመግዛት ትርጉም ያሳየናል እንዲሁም ...ወይቀንዩዎሙ ...አርባዕተ ምዕተ ዓመተ የሚለው ንባብ በባርነት መግዛትን ከሚያመለክቱ ገፀ ንባባት አንዱ ነው /4/

ከዚሁ ጋር አንድነት ያለው ሌላው ንባብ ..መንቅንዮ ለነዳይ በዕዳነ ወይኮንነ ምስኪነ ዘንክይድ ህየንተ አግፅኢነ .../5/የሚለው ነው።

www.ethiopianorthodox.org

በግዕዝ ሥልጣን ያለው ገዥ በባለሥልጣኑ የሚተዳደረው ሁሉ ደግሞ እንደተገዥ አድርጎ ያስቀምጣቸዋል። "በዓልክ ለኩሉ ነባሪ ወቀናይ ዕሪፍት ውእቱ፤ አይቴ ሀለው ቀነይት ወቅኑያን /6/ የሚለውና እሱን የመሰሉ ሁሉ የሚያመለክቱት ይኸው ነው።

እግዚአብሄርን ለማገልገል ተብሎ ራስን ዝቅ ማድረግን ራስን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማሰለፍና በእግዚአብሄር መንገድ ብቻ ተወስና መኖርን ለመግለፅ " ቀነየ " በሰፊው ይነገራል። በዚሁ መንገድ ከምናገኛቸው ዓረፍተ ነገሮች አንዱ ይህ ነው "....

እስመ እንዘ እግዚእ አነ እምኩሉ አቅነይኩ ርዕስየ ለኩሉ ከመእስተጋብእሙ ለብዙሐን ኀበ ሃይማኖት " /4/

ከጳውሎስ መልእክታት ይህን የመሰለ ብዙ መጥቀስ ይቻላል የቤተክርስቲያን አባቶች በፈቃዱ ለመልካም ሥራ የተሰለፈውንና ጊዜውን ሠውቶ በማስተማርም ይሁን በሌላ ባለው ችሎታ ለእግዚአብሄር ብሎ ነፃ አገልግሎትን የሚያበረክተውን ሁሉ አሁን ከተጠቀሰው ምንባብ ጋር የተያያዘ ስያሜ ይሠጠዋል።

"መቅነይ" የቀነየ አደራራጊ ሣልስ ቅጽል ነው ፤በመጽሐፈ ሲቃውንት ቃሉ ሲነገር እናገኘዋለን "ለከ ንትቀነይ ዘአንተ መቅነይ ለኩሎ" ይህ ዓረፍት ነገር በአደራራጊነት የሁለተኛ ደረጃ ገዥነትን ያመለክታል /8/ "ተቀነዩ ለእግዚአብሄር በፍርሐት ዘበጽድቅ ንትቀነይ ለከ የመሳሰሉት ዓረፍተ ነገሮች ሁሉ በንፁሕ ልቦና ለእግዚአብሄር መገዛትን ያመለክታሉ።

መፍጠር አፈጣጠር ለማለት በተለያዩ የግዕዝ መጻሕፍት ሲነገር ይገኛል /9/ በዚሁ አኳያ ለእጅ ሥራ አገልግሎት ስያሜም ይሆናል ይህን የሚጠቅሱ ጽሑፎች በመጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን እጅግ ጎልተው ይነገራሉ። " ... እምቅኔ እደዊ/ ትሁብ ለነዳያን ፤ ሥርዓተ ቅኔ ቤተክርስቲያን "የሚሉ ምንባቦች ከዚሁ ክፍል ናቸው /10/

ቀነየ ከሚለው ቀዳማይ አንቀጽ ካልአይ ዘንድ ትዕዛዝ ንዑስ አንቀፅ ሳድስ ቅጽልና ሳልስ ቅጽል እንዲሁም ባዕድ ዘርና ጥሬ ዘር ማውጣት የግዕዝ ሰዋስው ጠባይ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ የተዘረዘሩት ሁሉ ከአንድ ቀዳማይ አንቀጽ ቢወጡም የየራሳቸውን ትርጉም እየያዙ በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ሊገኙ ይችላሉ "ምቅናይ" የሚለው የቀነየ ባዕድ ዘር ቃል ራሱን ችሎ ለሁለት የተለያዩ ስያሜዎች ሲያገለግል እናገኘዋለን 1ኛ. በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በአደራረስ ጊዜ ጥሬ ዜማው ዝማሜው አንድ ላይ ምቅናይ ይባላል በዘመነ ስብከትና በዘመነ ዓቢይ ጾም ምቅናይ በቤተክርስቲያን በየሣምንቱ እሁድ ከመወደስ ቁመት በስተመጨረሻ ይደርሳል።

ቀነየ ባስደራጊነቱ የሰው ልጅ የሐጢአት ተገዥ ሲሆን ለሚያሳየው አቅዋም "አቅነይክሙ ርእሰክሙ ለሐጢአት ተብሎ ይነገራል /11/

ጥልቅ ምስጢር ምክር ምሳሌያዊ አነጋገር ያላቸውን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በሙሉ የቤተክርስቲያን መምሕራን ቅኔ ይሏቸዋል። እንደነሱ አባባል ጣዕም ባለው ዜማ መዘመርን ጨምሮ ባዲስ መልክ የሚዘጋጁ ወይም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ የሚሰጠው ግብራርያም ሆነ ስብከት ቅኔ ይባላል ካህናተ አሪት በመሰንቆም ይሁን በሌላ መሣርያ ያዜሙት የነበረው ሁሉ ስያሜው ቅኔ ነው። ሰብሕዎ ለእግዚአብሄር ስብሐተ ሐዲስ "የሚለው የግዕዝ ንባብ በአማርኛ ለእግዚአብሄር አዲስ ቅኔን ተቀኙለት" ተብሎ ተተርጉሞአል። በዮሐንስ 'ራዕይም ይህን የመሰለ የግዕዝ ምንባብ አለ እሱም እንደሚቀጥለው ይነበባል "...ወየሐልዩ ማሕሌተ ሐዲሰ ቅድመ መንበሩ ..." ወአልቦ ዘይክል አእምሮታ ለይእቲ ማሕሌት ዘእንበለ "እልክቱ አሠርቱ መ አርባዕቱ እልፍ መ አርብዓ ምዕት" የራዕየ ዮሐንሱ ግዕዝ በአማርኛ ቅኔ ተብሎ አልተተረጎመም በመሠረቱ ስብሐትና ማሕሌት ወደአማርኛ ሲለወጡ ምስጋና ተብለው ባንድ የሚጠቃለሉ ናቸው። ተርጓሚዎች ግን ስብሐት የሚለውን ቃል ቅኔ በማለት በአማርኛ ሲያስቀምጡት ማሕሌት የሚለውን ደግሞ ምሥጋና ብለውታል። /12/

ከአንድምታ ትርጉም ጀምሮ እስከነጠላ ትርጉም ከግዕዝ ወደ አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍትን መገልበጥ የተጀመረው ከአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ነው

www.ethiopianorthodox.org

ከጎንደር ዘመነ መንግሥት መዳከም ወዲህ ዘመነ መሳፍንት በተባለው ክፍለ ዘመን አንዳንድ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን በተናጠል የነጠላ ትርጉምን ሥራ አከናውነዋል፤ ለብዙ መቶ ዓመታት ተዳፍኖ የኖረው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ ዕድገት በዚሁ ወቅት እንደገና መጀመሩ የሚታወስ ነው ስለዚህ እነዚያ በተናጠል ተርጓሚዎቹ ምሥጋናንና ቅኔን ለአማርኛ ቋንቋቸው ተጠቅመውባቸዋል፤ ይህም ማለት አንዱ ምሥጋና በማለት ፋንታ ቅኔን ሲጠቀም ሌላው ቅኔ በማለት ፋንታ ምሥጋና ሲል ይገኛል። ይህ ብቻ አይደለም በግዕዝ ብካይ የሚለውን በአማርኛው ልቅሶ ማልቀስ አልቃሽነት ተብሎ መፈታት እንዳለበት ግልጽ ነው ቃል በቃል ከተተረጎመም መርዘምም ማጠርም የለበትም ከየትም ተፈልጎ አንዱ ቃል ባንድ ቃል ብቻ ነው መፈታት /መለወጥ/ ያለበት / በግዕዙና በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን ብዙ ልዩነት ይታያል ለምሳሌ ወበከየ ዳዊት ለሣኦል ወለዮናታን ወልዱ የሚለው የግዕዝ ንባብ፤ በአማርኛው ዳዊት ስለሣኦልና ስለልጁ ዮናታን ይህን የሐዘን ቅኔ ተቀኘ ተብሏል። ( ይህ፣ሐዘን) እነዚህ ሁለት ቃላት በግዕዙ የሉም።

ብዙዎች ይህንንና ሌሎችም መሠረት በማድረግ ሠቆቃውን፣ልቅሶውን ሁሉ ቅኔ ሊሉት ችለዋል። እዚህ ላይ ግን አንድ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት አገላለፅ እንዳለ ትዝ ሊለን የሚገባ ነገር አለ። በቅኔ ውስጥ ዘፈን ዝማሬ ግጥም ሌሎችም እንደታቀፉ እስካሁን አይተናል። ነገር ግን ምንም ለሥጋዌ ሆነ ለመንፈሳዊ ትምሕርት ሠጭነት የሌላቸው ለእንሥሣዊ ቅብጠት ብቻ የሚጋብዙና ምንም ጠቃሚ ዕውቀት የማይሠጡ ሁሉ ቅኔ ሊባሉ እንደማይችሉና በዚሁም የተሠማሩ ሁሉ ባለ ቅኔዎች እንዳይደሉ መታወቅ አለበት ዘፈን` የሚለው ቃል ግዕዝም አማርኛም ነው ስለዚህ ቃሉን በ5 ክፍለን ለማየት ይቻላል በቅድሚያ ግን በ4 የተዘፈለበትን መንገድ መመልከቱ ይቀላል። 4 የተባሉት ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ናቸው።

ሀ/ ሃይማኖታዊ ዕብራውያን በዘመነ ብሉይ ስውነታቸውን ሁሉ እያንቀሳቀሱ ምሥጋናቸውን ለአምላክ ያቀርቡ ነበር ዳዊትም የወገኖቹን ባህል አስገድዶት ጽላተ ህግ ከናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም በምትመጣበት ወቅት በጣም እየዘለለ ዘፈነ በዚህም ምክንያት ሜልኮል ናቀችው። ዳዊት በሚዘፍንበት ወቅት ባዶ እጁን አልነበረም የዘፈን መሣርያም ነበረው መሣሪያው በግዕዝ እንዚራ ይባላል። የግዕዙ ገፀ ንባብ ይህንን እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል "...ወርእየቶ ሜልኮል ለዳዊት ንጉሥ እንዘይዘፍን ወየአንዝር በቅድመ እግዚአብሄር ወመነነቶ ሜልኮል በልባ ...ወይቤላ ዳዊት ለሜልኮል እትዋነይኒ ወእዘፍንኒ ቅድመ እግዚአብሄር "

ዘፈንና ማሕሌት ልዩነት አላቸው ሥነ ሥርዓት ያለው ለዜማም ለአካል እንቅስቃሴውም ትምሕርት የሚያስፈልገው በጊዜያዊ ስሜት ሊዘምሩት የማይቻል ነው ማሕሌት በዘመነ ብሉይም በዕብራውያን ይካሄድ ነበር። ዕብራውያን ወደባቢሎን በተማረኩ ጊዜ በባቢሎናውያን የጽዮንን ማሕሌት አሳዩን ሲሉዋቸው የቤተእግዚአብሄርን ማሕሌት እንዴት በባዕድ አገር እናሰማለን ማለታቸውን ይህንን ያስገነዝባል "ሕልዩ ለነ ማሃልይሃ ለጽዮን እፎ ነሃሊ ማሕሌተ እግዚአብሄር በምድር ነኪር" ይላል። የግዕዝ ንባቡ ለመጀመሪያ ጊዜ የዜማን ሥርዓት ያቀነባበረው ቅዱስ ያሬድ ማሕሌታይ ይባላል እንጂ ዘፋኝ አይባልም ምክንያቱም የሱ ቅንብር ሥርዓት ያለው ብዙ ድካምን የሚጠይቅና ከማሕበረ መላዕክት ዝማሬ ጋር የሚገናኝ ልዩ ጣዕም ስላለው ነው። ካህናት በቤተክርስቲያን የሚያዜሙት ሁሉ ማሕሌት ይባላል ምዕመናን በጥምቀትና በሌሎች ክብረ በዓላት የሚያደርጉት ጭፈራ ሁሉ ደግሞ ዘፈን ይባላል እልልታና ሆታ በዘፈን ይጠቃለላሉ። ካህናት በማሕሌት ምዕመናን በዕልልታና በሆታ ለበዓሉ ክብር ድምቀት ሠጡት እየተባለ የሚነገረውም ከዚህ የተነሳ ነው። በአጠቃላይ ግን ሁለቱም ክፍል እግዚአብሄርን ለማገልገል ተብሎ ስለሚካሄድ ለእግዚአብሄር የቀረበ ምሥጋና ነው።

ለ . <u>ፖለቲካዊ</u> ፣ የፖለቲካ ሰዎች ፖለቲካዊ ዓላማቸውን ከሚያራምዱባቸው ዘዴዎች አንዱ ዘፈን ነው። ወለተ ሄሮድያዳ ሄሮድስ እንቲጳስን በፖለቲካዊ ዘፈን አስደስታ የዮሐንስ መጥምቅን ራስ አስቆረጠች። የፖለቲካ ዘፈን ከጥንት ጀምሮ ሠፊ ሥፍራ ነበረው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የተዘፈኑ የፖለቲካ ዘፈኖች እጅግ ብዙ ናቸው በተለይ ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ወዲህ ብዙ ፍቺ ያላቸው ዘፈኖች እንደተዘፈኑ

www.ethiopianorthodox.org

ዘገባዎች ያስረዳሉ። ዘመናዊው ሬዲዮ ከሚያሰራጫቸው ዘፈኖች አብዛኞቹ የፖለቲካ ዘፈኖች ናቸው።

ሐ <u>ኢኮኖሚያዊ</u> :- በጥንት ዘመን ኢኮኖሚ በኩል ዘፈን ምን ድርሻ እንደነበረው በቀላሉ ለማወቅ አልተቻለም ባለንበት ዘመን ግን ዘፈን ለኢኮኖሚ ዕድገት ቅስቀሳ እጅግ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል። በተለይ በኢትዮጵያ ከ66 ዓ/ም ወዲህ ዘፈን እንደ ትምህርት ተወስዷል በሬድዮና በቴሌቪዥን የሚተላለፉ የዘፈን ቅስቀሳዎች ከፍተኛውን ሥፍራ ይዘውት ይገኛሉ።

መ. <u>ማሕበራዊ</u>:-ሕብረተሰብ የሆነ ሁሉ የራሱ የሆነ ባህል አለው ከባህሎቹም አንዱ ዘፈን ነው። ማሕበራዊ ኑሮውን በተለያዩ ዘፈኖች ያንፀባርቃሉ። የትኞቹ በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ እንደሚጠቅሙ የትኞቹ እንደሚጎዱ ሕብረተሰቡ ሁሉ በዘፈን ይገልጸል፤ በየባላገሩ ለማሕበራዊ ኑሮ እጅግ ጠቃሚ ዘፈኖች ከጥንት ተያይዘው የመጡ ይሰማሉ ብዙዎች በዘመናዊ ማስሚድያ ስለሚተላለፉ ልብ ብሎ መከታተል ከተቻለ ብዙ ዕውቀት ሊገበይ ይችላል። ብዙ የኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች ቋንቋዎችን የመስማት ችሎታ ያለው ሰው ሩቅ ሳይሄድ ከቤቱ ቁጭ ብሎ በማየትና በመስማት ብዙ ዕውቀትን ሊገበይ ይችላል። ከግዕዝ ከአማርኛ ከትግሪኛ እንዲሁም ከውጭ ቋንቋዎች ብዙ የባህል ዘፈኖችን ለማስረጃ ያህል መጥቀስ በተቻለ ነበር ነገር ግን ይህን ያህል አስፈላጊ መስሎ አይታይም።

ሠ. <u>ኢህጋዊ ዘፈን</u>፣ ከዚህ በላይ የተገለፁት የዘፈን ዓይነቶች በሕብረተሰብ ኑሮ ውስጥ የግድ ነው። በተለይ በፊደል ለ ፣ ሐ ፣ መ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው ትምህርት ሰጭነታቸውም ከፍተኛ እንደሆነ አይካድም። ግን ከነዚህ ሁሉ ምንም ግንኙነት የሌለው የዘፈን ዓይነት አለ ይህም ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ኢህጋዊ ዘፈን ነው። ለጊዜው ሌላ ስያሜ ስላልተገኘለት በተጠቀሰው ስም ብቻ ለመጠቀም የግድ ሆኗል። የዚህ ዓይነት ዘፈን ሠካራምነትን ዘማዊነትን ርኩሰትን መዳራትን ጣኦት ማምለክን ሙዋርትን ጥል ክርክር ቅንዓትን ቁጣን አድመኛነትን መለያየትን መናፍቅነትን ምቀኝነትን መግደልን ያቀፈ ነው። ስለዚህ በቤተክርስቲያንም ሆነ በሕብረተሰብ ፈጽሞ የተጠላና የተወገዘ ነው። ሌሎችም ሙሉ በየዳንስ ቤቱ አሸሸ ገዳሜ በማለት ራሳቸውን ወደከዊነ እንሥሣ የለወጡ ግለሰቦች የሚጨፍሩበት የዘፈን ዓይነት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል። በግዕዝ ቋንቋ ዳንስ የሚለው ቃል ከእግዚአብሔር መንገድ የወጡ ሰዎች የሚፈፅሙት ተግባር ነው። ከሁሉ በይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ ዳንስ ቤት ከፍተው የሚነግዱ ሰዎች ክርስቲያኖች ነን ባዮች ናቸው። ለከፍተኛ የክርስቲያናዊ ሥነምግባር ጉድለት ዓይነተኛ ምክንያት ለሆነው ለዚሁ ርካሽ ዓላማ ሰዎችን እየጋበዙ በሞራል ውድቀት ማንነታቸውን ከዘነጉ በኃላ በሚሰበስቡት ሐብት እየተንደላቀቁ ክርስቲያንነት ሊኖር ፈፅሞ አይችልም።

ከ-ሠ ድረስ ስንት የዘፈን ዓይነቶች እንዳሉ ተዘርዝሯል ከለ-ሠ ድረስ የተዘረዘሩት የዘፈን ዓይነቶች ከቅኔ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም በፊደል ሀ የተገለጸው የዘፈን ዓይነት ብቻ ነው ከቅኔ ጋር ግንኙነት ያለው ምክንያቱም ይህ የዘፈን ዓይነት በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ የኖረ አሁንም ያለ ለወደፊትም በቤተክርስቲያን ተጠብቆ ሊኖር የሚገባው የመንፈሳዊ አገልግሎት አንዱ ክፍል ስለሆነ ነው።

አምልኮተ እግዚአብሔርና ቅኔ የተለያዩ አይደሉም ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተቀነዩ ለእግዚአብሔር ወፀውዑ ስሞ ወለከ ይትቀነይ ኩሉ ልሣን እነዚህ ሁሉ የሰው ልጆች ያላቸውን በእግዚአብሔር ፈቃድ የመመራት ሁናቴ የሚገልፁ ናቸው ቅዱስ ጳውሎስ በሰዎች መካከል የገዢና የተገዢ ደረጃ እንዳለ አልጻፈም በሰዎች መካከል ያዛዥና ታዛዥደረጃ እንዳለ ግን ጽፏል። ዓለም በመንግሥታት ትመራለች መንግሥት ማለት ደግሞ ሕዝብ ነው። መንግሥቱን የሚመራ የበላይ ሰው ይኖራል መሪው ሕዝቡን እንዲገዛ ሳይሆን በመንግሥቱ ህግ መሠረት ሕዝቡን

እንዲያስተዳድር ብቻ ይፈቀድለታል። ሰዎች በቅኔ ሰዎችን ያሞግሳሉ ሰዎችን ያጥላላሉ ግን ይህ ሁሉ ፍፁም ስህተት ነው የሥርዓተ ዓመልኮትን ዓላማ ይቃረናል።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በጽርዕ ቋንቋ ሥርዓተ አምልኮትን ስታካሂድ ከቆየች በኃላ ከስድስተኛ መቶ ክፍለ

www.ethiopianorthodox.org

ዘመን ጀምሮ በግዕዝ ቋንቋ መጠቀም ጀመረች ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለብዙ መቶ ዓመታት የራሷ ዜማ አዘጋጅታ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚካሄዱ ብዙ የዜማ ዓይነቶች እንዲኖሩአት ሆኗል ግን በአገልግሎቱ ውስጥ አሁን ያለው የቅኔ አቀራረብ አስፈላጊ አልነበረም ድጓው ራሱ የተሟላ ዝግጅት አለው። ስለዚህ በድጓው የሠፈረው ብቻ በጥሬ ዜማ ወይም በዝማሜ እየተዘመረ ይታለፍ ነበር። ባሁኑ ጊዜም ቢሆን እንኳ ግጥሙ ቅኔ ቢኖርም ባይኖርም ከጥንቱ ሲያያዝ በመጣው መሠረት ስብሐተ ነግህና አርያም የሚካሄድባቸው በዓላት አሉ ለምሳሌ መጋቢት መሥቀልና መጋቢት በዓለ እግዚአብሔር ስብሐተ ነግህ፣ ነሐሴ አንድ ቀን (ደናግል)ና ነሐሴ አሥር ቀን (ማሕበር) አርያም ሲደርስ የቅኔ መኖር ሳያስፈልግ ይካሄዳል። (መም. ሀረገ ወይን ገ/ማርያም) በአጠቃላይ ቅኔ ማለት ዜማ ነው ወይትቀነዩ ካህናት በዜማ የሚለው ይህን ያስረዳል።

ብዙዎች የኢትዮጵያ ታሪክ ዘጋቢዎች ቅኔን የጀመረ ቅዱስ ያሬድ ብቻ እንደሆነ ይስማሙበታል ድጓ በግጥምና በስድ ንባብ የተቀነባበረ ነው። የቅኔን ስያሜ የያዙ ዝግጅቶች በድጓ ውስጥ ይገኛሉ የቅኔ በቅዱስ ያሬድ መጀመር በሁለት ተከፍሎ ይነገራል ጠቅላላ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች በሙሉ ቅኔዎች ናቸው ምክንያቱም ዜማው ስድ ንባቡና ግጥሙ በነሱ ውስጥ ተካትተው ይገኛሉና የሚለው አንደኛው ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመወድስ የሚበዝኑ በዋዜማ በዘይዕዜ በክብር ይዕቲና በዕጣነ ሞገር ስያሜ ብቻ የተቀመጡት ቅኔ ይባላሉ የሚለው ነው።

## የቅኔ ትምህርት አጀማመር

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥንታዊው መንፈሳዊ አገልግሎት እንዴት ይካሄድ እንደነበር ከመጽሐፈ ኪዳን ክፍል አንድ መረዳት ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ስብከትና ትምህርት ማሕሌትና ቅዳሴ የየራሳቸው የሆነ ክፍለ ጊዜ እንደነበራቸው በግልጽ ያስረዳል። እንደ መጽሐፉ አመዘጋገብ እሁድን ጨምሮ መንፈሳውያን በዓላት በተከበሩ ቁጥር ማሕሌቱ ስብከቱና ትምሕርቱ በቅደም ተከተል ይካሄዱ ነበር። ማሕሌቱ ተጀምሮ መካሄድ ሲጀምር በየጣልቃው እንደየምሥጢሩ ከብሉያትና ከሐዲሳት ምንባቦች ይነበባሉ የተነበበው ምንባብ እንዲሁ አይታለፍም ለሕዝቡ በሚገባው ቋንቋ ይብራራል ማሕሌቱና ትምሕርቱ ሲያበቃ ሥርዓተ ቅዳሴ ይጀመራል በማሕሌቱና ሥርዓተ ቅዳሴው ንዑሰ ክርስቲያን የተባሉት ይካፈላሉ። የሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎት የሚካሄደው ለንዑሰ ክርስቲያኖች ተብሎ ነው። በሥርዓተ ቅዳሴው የሚነበቡ መልእክታት ግብረ ሐዋርያትና ወንጌል ገለፃ ይደረግባቸዋል ምክንያቱም የነሱ ትምሕርት በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ መነበብ ለንዑሰ ክርስቲያኖች ትምሕርት ማግኘት ተብሎ ስለሆነ ነው ከሥርዓተ ቅዳሴው በስተመጀመሪያ የመጣው መባ ሁሉ ይሰበሰባል መባው ለቅዳሴ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች ብቻ የሚያጠቃልል ነው መባው ተሰብስቦ ሲያበቃ አንድ ዲያቆንና አንድ ቄስ ልብሰ ተክህና ለብሰው ወደ ተሰበሰበው መባ ይመጡና ዲያቆኑ ፀልዩ በእንተ እለ ያበውዑ ሲል "ቄሱ ፀሎተ መባዕን ያነባል።

ሥርዓተ ቅዳሴው ሲያበቃ ፃኡ ንዑሰ ክርስቲያን ብሎ ዲያቆኑ ያውጃል ንዑሰ ክርስቲያኖችም ይወጣሉ በዚህ ጊዜ ቅዳሴው ይጀመራል። የቅዳሴው አጀማመር እንዴት እንደነበር ገና በጥናት አልተደረሰበትም ምናልባትም "ሚመጠን" በዚህ ጊዜ ይባል ኖሮ ይሆናል የሚል ግምት አለ። ንዑሰ ክርስቲያን ከሌሉ ሥርዓተ ቅዳሴን የማያደርሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ዶክተር ሥርገው ሐብለ ሥላሴ በሕትመት ላይ ባልዋለው መዝገበ ቃላት ጽሑፋቸው ያስረዳሉ።

በኛ ቤተክርስቲያን ሥርዐተ ቅዳሴና ዋናው ቅዳሴ አንድ ላይ እንዲካሄዱ ቀስ በቀስ እየተለመደ መጣ

www.ethiopianorthodox.org

የተጀመረበት ዘመን ባይታወቅም ከ13ኛና ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ እንደሆነ ይገመታል ስዓታት በ14ኛው ክፍለ ዘመን ስለተጀመረ በማሕሌት ላይ ለውጥ ተጀመረ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ የቅኔ ትምህርት ተጀመረ።

ስለቅኔ አጀማመር በኢትዮጵያውያን መምሕራን በኩል ሁለት የተለያዩ የታሪክ ዘገባዎች አሉ። በአንደኛው ክፍል አሁን ያለው የቅኔ መንገድ የተጀመረው በዮሐንስ ገብላዊ ነው የሚል ሲሆን በሁለተኛው ደግሞ የአሁኑን ቅኔ የጀመረው ደቀ እስጢፋ የተባለው ሰው እንደሆነ የሚገልጽ ነው ሁለቱንም ክፍሎች በቅደም ተከተል ከዚህ ቀጥሎ ይታያሉ።

1. <u>ዮሐንስ ገብላዊ</u>:-ይህ ምሁር ዮሐንስ ፍልሱፍ በመባልም ይጠቀሳል ይህ ቅጽል ሊሠጠው የቻለው በምሥጢር እየተራራቀ ቅኔን ስላስፋፋ እንደሆነ መገመት አያዳግትም ገብላዊ የተባለበት ምክንያት ደግሞ ዋድላ ድላንታ ውስጥ በምትገኘው "ገብላት" በምትባል ቀበሌ ስለተወለደ ነው። ዮሐንስ ገብላዊ 1427–1460 'ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ቅኔን እያስተማረ ኖረ።

ከሱ ተማሪዎች መካከል አባ ወልደ ገብርኤል የተባሉ መነኩሴ ይገኙባቸዋል አባ ወልደ ገብርኤል ዮሐንስ ገብላዊን ተክተው ቅኔን አስተምረዋል /እሱ ከሞተ በኋላ ማለት ነው/ከአባ ወልደ ገብርኤል ሞት በኋላ ደግሞ ሠምረ ክርስቶስ በጉባኤው ተጠለበት ሠምረ ክርስቶስ በቅኔ መምሕርነት አሥር ዓመት ቆይቷል ይኸውም ከ1460–1470 ዓ.ም ድረስ መሆኑ ነው። ዓፄ ባዕደ ማርያም የተባሉ ንጉሥም ልክ እንደ ሠምረ ክርስቶስ በንጉሥነት አሥር ዓመት ብቻ ነው የቆዩት አፄ ባዕደ ማርያም ከሠምረ ክርስቶስ ጋር ተጣልተው ነበር። የተጣሉበት ምክንያት የቅኔ ባዲስ መልክ መቅረብ በሳቸው ዘንድ አዲስ ነገር በመሆኑ ነው። ነገር ግን ባዕደ ማርያም የግዕዝን ስዋሰው ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበር ሁኔታውን ባጭር ጊዜ ውስጥ ተረድቶ ሁለቱ ሊታረቁ ችለዋል። ሁለቱን ያስታረቀ ቅኔ "ድሕረ ተሠብረ እጽንየ ለልቡናየ ልሁኩት..." ለሚለው ጉባኤ ቃና እንደሆነ ይነገራል።

ድድቅ ወልደ ማርያምና ተዋናይ የሠምረ ክርስቶስ አራተኛ ትውልድ መሆናቸው የጸፉ ባለ ታሪኮች አሉ እንደነሱ አመዘጋገብ ሁለቱ ድድቅ ወልደ ማርያምና ተዋነይ ካንድ



ት/ቤት የወጡ ናቸው ከይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት መዲና አማራ ሳይንት ነበር ከዮሐንስ ገብላዊ ጀምሮ እስከተዋናይና ድድቅ ወልደ ማርያም ድረስ የነበሩ የቅኔ መምህራን ከአማራ ሳይንት አካባቢ አልራቁም ነበር ከዚያ ወዲህ ግን ግራኝ መሐመድ ሲነሳ ድድቅ ወልደ ማርያም ወደ ጎንደር ሄዶ ዳውንት ውስጥ ጨረታ ሚካኤል በተባለው ደብር ቅኔን እያስተማረ ተቀመጠ ተዋነይ በበኩሉ ወደ ጎጃም በመሄድ እዚው ቅኔን አስፋፋ።

2. <u>ደቀ እስጢፋ</u> ደቀ እስጢፋ ግሪክ ሄዶ ፍልስፍናን ተማረ የተማረውም የፍልስፍና መንገድ ከቅኔ መንገድ ጋር የሚመሳሰል ነው። ስለዚህ በፍልስፍናው ባገኘው ዘዴ ተጠቅሞ የቅኔውን መንገድ ፈለሰፈ የሚሉ አሉ። ደቀ እስጢፋ ከ1470–1486 ባለው ጊዜ ውስጥ እንደነበር ይታመናል። ደቀ እስጢፋ ቅኔን ማስተማር ሲጀምር አፄ ባዕደ ማርያም በሕይወት ነበሩ ። አፄ እስክንድር ከሱ ቅኔን ተምረዋል።

አንድ ኢትዮጵያዊ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ግሪክ ሄዶ ተማረ ማለት ያስቸግራል። ቱርኮች ከዚያ በፊት ጀምሮ ለብዙ ዘመናት ግሪክን በመቆጣጠር ላይ ነበሩ። ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን ለመውረር የቻለው ከነሱ የመሣሪያ ድጋፍ ስላገኘ ነው ብዙ የሜድትራንያን አካባቢ አገሮችን በቁጥጥር ከማዋል አልፈው የኢትዮጵያ ጠረፎች የነበሩት የቀይ ባሕር አካባቢዎች በነሱ እጅ ወድቀው ነበር። የግሪክ የፍልስፍና ት/ቤቶችም በዚህ ወቅት ከተዘጉ ዘመናትን አሳልፈው ነበር። ስለዚህ እነዚህና ሌሎችም ምክንያቶች እያሉ ከኢትዮጵያ ተነስቶ አንድ ኢትዮጵያዊ ግሪክ ድረስ ሄዶ ሊማር አይችልም። ደቀ እስጢፋ ወደ ጎጃም የሄደበት ምክንያት በንጉሡ ሚስት ስለታማና ንጉሡም ስለጠረጠሩት በሽሽት መሆኑ ይነገራል። ሆኖም፤ በጎጃም ቅኔን አስፋፍቷል።

የቅኔ ቦታዎች ከ15ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ለሁለት ምዕት ዓመታት የዋድላና የጎጃም በመባል በሁለት ተከፍለው ቆዩ፤ ቆይቶ የጎጃም የቅኔ ቦታዎች የዋሸራና የጎንጅ በመባል ለሁለት ተከፈሉ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የጎንደር ከተማ ስትቆረቆር አራተኛው የቅኔ ቦታ በዚችው ከተማ ተስፋፋ ከዚያ



www.ethiopianorthodox.org

ወዲህ የቅኔ ቦታዎች አራት ሆኑ። የአራቱ ክፍሎች የቅኔ መንገድ ይለያያል።

ቅኔ ከልብ ሠርጾ ሲገባ የግድ ወደብቸኝነት ኑሮ ይስባል ቅኔ በሚቀነባበርበት ጊዜ እጅግ ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ ማግኘት የግድ ይሆናል ካልሆነ ደግሞ አካባቢው ጭር ሲል ሌሊቱን ሙሉ እያሰላሰሉ ማደር ይመረጣል። በመንገድ ጊዜም ቢሆን አብሮ ተጓዥ ጓደኛን ያስጠላል ምክንያቱም በሁለቱ ጨዋታ ስለሚናር ነው። በአጠቃላይ ቅኔ የብሕታውያን ሞያ ነው ማለት ይቻላል፤ በቅኔ ባለሙያነት የተካኑ ብዙ ሰዎች በተባሕትዎ ተወስነው ለመኖር ይገደዱ ነበር። የቅኔን ሞያ ካስፋፉ የጎንደር መምህራን መካከል ክፍለ ዮሐንስ አንዱ ነው። ይህ የቤተክርስቲያን ምሑር ከአክሱም ከተማ በስተሰሜን ምስራቅ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብላ በምትገኘው "ማይሩባ" በምትባለው አጥቢያ ተወለደ ማይሩባ ቅዱስ ያሬድ ከተወለደበት መደባይ ወለል ጎድን ትገኛለች ሁለቱ ቦታዎች /መደባይ ወለልና ማይሩባ /በዘመነ አክሱም ብዙ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የወጡባቸው መሆናቸው ይታመናል።

ክፍለ ዮሐንስ የ4ቱ ጉባዔያት ባለቤት ከመሆኑም በላይ የቅኔን መንገድ ለማስተካከል ብዙ የጣረ ምሑር መሆኑ ይነገርለታል። ኑሮው በብሕትውና የተወሰነ ነበር። እንዲያውም አልባሌ መስሎ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር ከቆየ በኃላ የመጋቢት መድሐኒዓለም ዕለት ጎንደር ከተማ በሚገኘው የመድሐኒዓለም ደብር የመወድስ ቅኔ በመቀኘቱ ዕውቅና ማግኘቱን አንዳንድ የቤተክርስቲያን መምሕራን ያስረዳሉ። የመድሐኒዓለም ዕለት የተቀኘው መወድስ ቅኔ "ጣዕዋ ንዑስ መድሐኒዓለም" የሚለው ነው ቅኔው ክርስቶስ መልዕልተ መስቀል የተቀበለውን መከራ ምሥጢር ይገልፃል። ከዚህም ሌላ የእሱ ቅኔዎች በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምሕራን ዘንድ በብዛት ሲነገሩ ይሰማል ከጉባዔ ቃና እስከመወድስ ለፀናዕል ትምሕርት በቋሚነት ተመድበው የሚገኙት ሁሉ የእሱ ቅኔዎች ናቸው። አሁን ያለው የቅኔ ዜማ በሙሉ የተወሰነው በእሱ አማካይነት ሳይሆን እንዳልቀረ ይታመናል። ክፍለ ዮሐንስ በአፄ አድያምሰገድ ኢያሱና በአፄ ዳዊት ዘመን እንደነበር ከተቀኛቸው ቅኔዎች ለመረዳት ይቻላል።



ክፍለ ዮሐንስ ከካህናት ጋር ብዙም ተግባቢነት የነበረው አይመስልም። ካህንና እረኛን፣ ቤተመቅደስንና የእንስሶች በረትን፣ በመነሻነት ይወስድና በካህናት ያለው ተንኮል በእረኞች እንደሌለ ቤተመቅደስም የወንበዴ ቦታ ልትሆን እንደቻለች ይህም ይታወቅ ዘንድ ጌታችን በቤተ ልሔም ዋሻ በተወለደ ጊዜ እረኞች ከሰማይ መላእክት ጋር ሲዘምሩ እንደታዩ በቅኔው ገልጿል።

ቅኔውም በከፊል ይህ ነው። "እምክዊን ካህን ይኄይስ ከዊንኖላዊ ወኀለ እንስሳ ትትበደር እምቤተመቅደስ ዐባይ እስመቤተመቅደስ ኮነት ቤተፈያታይ ወበላእለኖሎት ኢሀለወ ላዕለ ካህናት ዘሀሎ ዕከይ..."

የዋድላና ፣የጎንጅና የዋሸራ መምህራን ለግዕዝ ሰዋሰው መመሪያ ሊሆን የሚችል ዝግጅት በየራሳቸው አዘጋጅተው ትተዋል። ይህም መመሪያ በነሱ አባባል አጠቃላይ ስሙ አገባብ ይባላል። በዝርዝር ሲነገር ደግሞ እርባትምር ፣ ዐቢይ አገባብ፣ንዑስ አገባብና ደቂቅ አገባብ ይባላል። ዋድላዎችና ዋሸራዎች ሆን ብለው አገባቡን ትምሕርት ይሠጡበት ነበር ወደ ቅኔው ይህን ያህል ትኩረት ሳይሰጡ በይበልጥ አገባብን በማስተማር የታወቁ መምሕራን ነበሩ። ለምሳሌ ያህልም በደቡብ ጎንደር የኔታ መርሻ ፣ የኔታ ብዙአየሁ በሰሜን ጎንደር በአገባብ አስተማሪነታቸው የታወቁ ነበሩ። የደቡብ ጎንደሩ የኔታ መርሻ ፍፁምነት የነበራቸው ባህታዊ ስለነበሩ ማሕበረሥላሴ ገብተው ገዳማዊ በረከትን በማግኘት በዚያው አርፈዋል።

የአገባብ መምህራን ባንድ በኩል የራሳቸውን ቋሚ ተማሪዎች እያስተማሩ በሌላ በኩል ከሌሎች መምህራን ለቅኔ መምሕርነት የበቁትን መምሕራን አገባብ ያስተምሩ ነበር በዋድላው የቅኔ መንገድ ለቅኔ መምሕርነት የበቃው ደቀ መዝሙር እንደገና ወደ ጎንጅና ወደዋሸራ የአገባብ መምሕራን ሄዶ የእነሱን የአገባብ መንገድ ይማራል የጎንጅና የዋሸራ የቅኔ ምሩቃንም ወደዋድላ የአገባብ ሊቃውንት በመሄድ የነሱን የአገባብ መንገድ ያጠኑ ነበር።

የጎንጅ የቅኔ መምሕራን ይህን ያህል የጽሑፍ አገባብ አላስተላለፉም የነሱ የአገባብ ትምሕርት አብሮ ከቅኔው ጋር



www.ethiopianorthodox.org

ነው የሚሰጠው ከጎንደ የቅኔ መምሕራን የተማሩ ሁሉ የጽሑፍ አገባብ እንዲኖረው አይገደድም የአገባቡን መንገድ ከቅኔው ትምሕርት ጋር በሚገባ ያውቀዋል ስለአገባብ መንገድ ቢጠየቅ መጽሐፍ ልመልከት ሳይል ወድያውኑ መልስ ይሰጣል ባንድ ቅኔ ውስጥ መወድስም ይሁን ሌላ የጎንደ ቅኔ ሲነገር በአገባብ ስለሚቀነባበር ላላወቀው ሰሚ በጣም ይከብዳል። ሁሉም የአገባብ አይነቶች ይኖራሉ ስለዚህ የቅኔውን ምስጢር ከተረዳ በኋላ ቀጥሎ ይህ አብይ አገባብ ነው ይህ ንዑስ ነው ይህ ደቂቅ ነው እያለ በአእምሮው ያስገባዋል። ቅኔንም ለመቅረፅ በስፊው ይረዳዋል። በአጠቃላይ የግዕዝ ሰዋሰው የሞያ ጥንቃቄ በጎንደ የቅኔ መምሕራን ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ አለው በነሱ ያለው ትንሽ ችግር የግዕዝን ቃላት እንደልብ ለመጠቀም አለመፍቀድ ነው። የግዕዝ ቋንቋ በቋንቋነቱ ብቻ በነሱ ዘንድ በሥራ ላይ አይውልም ብዙዎች የግዕዝ ቃላት የአማርኛ ፀያፍነት አላቸው እየተባለ በቅኔ እንዳይገቡ ይከለከላሉ ይህ አባባል ስህተት እንደሆነ ይታወቃል ምክንያቱም ማንኛውም ቋንቋ በሌላ ቋንቋ ከታረመ ሂደቱን ስለሚያበላሸው ነው። የጎንደር የቅኔ መምህራንም በጽሑፍ የሠፈረ አገባብ የላቸውም እነሱ ይጠቀሙ የነበረው ከላይ በተጠቀሱት ክፍሎች አገባቦች ነው ቅኔያቸውም ቢሆን የሰዋሰውን መንገድ የሚጠነቅቅ አይደለም ዋናው ትኩረታቸው የመጻሕፍትን ምሥጢር በቅኔ መግለፅ ነበር። ከብሉያትና ከሐዲሳት ትርጓሜ ጋር ቅኔን ያያይዙታል። ይህ የሆነበት ምክንያት በጎንደር ለመጀመሪያ ጊዜ የመጻሕፍት ትርጉም በአማርኛ ሲዘጋጅ ቅኔም ከዚያው ጋር አብሮ በመስፋፋት ላይ ስለነበር ነው።

## የቅኔ ለተለያየ ስሜት መግለጫ መሆን

ከ15ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ቅኔ ምሥጋናን ጸሎትን መዝሙርንና ሌሎችንም የሥርዓተ አምልኮት ክፍሎች መግለጫ ብቻ ሆኖ ቆይቶ ነበር። ኢትዮጵያውያን የቅኔ ተመራማሪዎች መነሻቸውና መድረሻቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ነበሩ። እየቆየ ግን ሌላ መንገድ ተፈጠረ ይኸውም ቅኔን የግል ስሜት መግለጫ የማድረጉ ተግባር ነው። በ15ኛው ክፍለ ዘመን በደቀ እስጢፋና በአጼ እስክንድር መካከል ያለመግባባት ስለተፈጠረ ሁለቱም የየግላቸው ስሜት መግለጫ ቅኔ እንደተቀኙ ይነገራል በነሱ ስም የሚጠቀሱ ቅኔዎች አሉ ግን የነሱ ይሁኑ የሌላ ጥናት አልተካሄደባቸውም በቅኔ እርስ በእርስ መነቃቀፍ የተጀመረው በ17ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡ ይህ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናት ለሦስት የተከፈሉበት ጊዜ ነበር። በካቶሊኮች ምክንያት በኢትዮጵያውያን መካከል አሰቃቂ የደም መፋሰስ መፈጸሙ የሚታወስ ነው። የካቶሊኮች ጣልቃ ገብነት በፖለቲካና በሃይማኖት በቀላሉ የማይሽር ጠባሳ በኢትዮጵያውያን ላይ ጥሎ አልፏል።

ፀጋ ቅብዕትና ካራ የሚሉ የክፍፍል ስሞች የመነጩት በዚህ ጊዜ ነው። ይህ የሃይማኖት ክፍፍል ለሁለት ምዕት ዓመታት የሐይማኖት ጠርነት እያስነሳ ቆይቶአል። መከፋፈሉን ያስፋፋት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምሕራን አንዱ በሌላው ላይ ይሠንዝሩት በነበረው ነቀፋ ነው። ነቀፋው የሚገለፀው በቅኔ ነበር ከያንዳንዱ ክፍል ብዙ ቅኔዎች ለትችትና ለነቀፋ ውለዋል። ከነሱም ብዙዎቹ ተመዝግበውና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፈው ያሁኑ ትውልድ እንዲመለከታቸው ሆነዋል።

ቅኔ የሚለው ስያሜ ትርጉም ያጣው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ለሁለት መቶ ዓመታት ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምሕራን በዚሁ ተግባር ተጠምደው ኖሩ`የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ መሆኑ ይታመንበት የነበረው ቅኔ ለማይጠቅምና በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ምንም አገልግሎት ለማይሰጥ እጉል ፍልስፍና እንዲውል ተደረገ። ከዚህ አልፎ ደግሞ የማንነት መታወቂያ ሆነ ነገሥታት መሳፍንትና መኳንንት በቅኔ እየተወደሱ እየተመሰገኑና ሐረገ ትውልዳቸው ሳይቀር እየተቆጠረ የከንቱ ውዳሴ ተገዥዎች ብቻ ሆነው ቀሩ። ከደብር ዕልቅና ጀምሮ ያሉት የቤተክርስቲያን የሥራ ምድቦች አብዛኛውን ጊዜ ይሰጡ የነበረው የመንግሥትን ባለሥልጣናት በቅኔ ለሚያሞግሱ ግለሰቦች ነበር። ይህ አድራጎት ቤተክርስቲያንን በብዙ መንገድ ጎድቶአታል። የብዙዎች ኢትዮጵያውያን ካህናት ዓላማ ቅኔ ተምሮ ቅኔን ለባለሥልጣኖች በማበርከት ለሥልጣን መብቃት ሆኖ ቀረ። ይህም ሆኖ የቅኔን ለአልባሌ ተግባር ማዋል አላስፈላጊነት የተረዱ አባቶች እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አልጠፉም ነበር። የሚቀኙት ቅኔ

www.ethiopianorthodox.org

እጅግ ተጠበውና ተጨንቀው ሱባዔም ገብተው የመንፈስ ቅዱስ ረዳትነትንም ጠይቀው የሚያቀርቡት እንደነበር ግልፅ ነው። ለቅኔ ባለሞያዎች የተሰጠ ያላስፈላጊ ቃል አለ ይህም "ዘራፊ" የሚለው ነው። በዚህ ቃል እየተመሩ ብዙዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሲያታልሉ ይታያል ምንም ሳናስብ ሳንቆጥርና ሳናቀናብር ከመቅጽበተ ዓይን ቅኔውን እናወርደዋለን ይላሉ እነባበባቸው የግዕዝም ሆነ የአማርኛ ቋንቋ ለዛ የለውም ወዲያና ወዲህ በመወራጨት የሚያሰሙት ጩኸት እጅግ ይዘገንናል ምናልባትም ቅኔን ለማያውቅ ሰው ሁኔታው እውነት ይመስለው ይሆናል "ዘራፊ" የሚለው ቃል ባልባሌነት የኋላ ኋላ የመነጨ ይመስላል ይህ ቃል የውንብድናን ተግባር ለሚያከናውኑ ግለሰቦች የሚውል ስለሆነ ከቅኔ ጋር ምንም ግንኙነት ባይኖረው ይመረጣል።

የአማርኛ ቋንቋና የግዕዝ ቋንቋ የራሳቸው የሆነ ጠባይ እንዳላቸው ይታወቃል። በከተማችን የምንሰማው አብዛኛው በቅኔ ስም የሚነበበው ግን የቅኔን የዜማ ልክ በመያዙ ብቻ ቅኔ ይባላል እንጂ ቅኔ አይደለም። ይህ ነው ተብሎም ስም ሊሠጠው አይቻልም። እንዳጋጣሚ ሆኖ እውነተኛውን ቅኔ የያዙ ሰዎች በትክክል ቅኔውን ቢያነቡ "ያንተ ቅኔ ለአደባባይ የማይገባ ጣዕም የሌለው ነው" ተብለው በግልፅ ይተቻሉ። ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ ተችዎቹና ነቃፊዎቹ ፈፅመው በሞያው የሌሉበት ናቸው። ድጋፍ ሰጭዎች ቅኔውን የሚያነበው ሰው ያለቅጥ የሚያሳየውን የአካል እንቅስቃሴ ተመልክተው ሳቅና ጭብጨባ ያስተጋቡለታል። የቅኔውን ሞያ ጠለቅ ብለው የተረዱ ምሑራን በዚሁ ጊዜ ሐዘንና ፀፀት ይሰማቸዋል ምክንያቱም ድፍረትና ሐሰት ተደምረው ትልቁን የቤተክርስቲያን ሞያ ሲያዳፍኑት ስለሚያዩ ነው።

አብዛኛው በየአደባባዩም ይሁን በየቤተክርስቲያኑ የሚነገረው ቅኔ ከአማርኛ ተቀርፆ ወደግዕዝ የተለወጠ ነው። ይህ ዓይነቱን ቅኔን የሚቀኙትን ሰዎች ከተቀኙት ቅኔ መካከል አንዲት ቃል ቢጠየቁ "በአማርኛ እንዲህ ይባላል" የሚል መልስ ይሠጣሉ የግዕዝን የስዋሰው መንገድ በፍፁም አይነኩትም። ይህ መሰሎቹ ግለሰቦች የቅኔ ሊቃውንት ናቸው እያሉ በቤተክርስቲያን ግሕተምና በኃላፊዎች ፊርማ እየመሰከሩ የሚልኩዋቸው ስለቅኔም ይሁን ስለግዕዝ ቋንቋ



አካሄድ ምንም ያልተረዱ ናቸው። ይህ ድርጊት በሁለት በኩል ስህተት እንዳለው ያመለክታል አንደኛው ለትልቁ ሞያ ዋጋ ማሳጣት ሲሆን 2ኛው በሐሰት መመስከሩ ነው ።

ባልዋሉበት ሞያ መመስገንና መክበር ራስን ያስረሳል ወደ ከባድ ስህተትም ይጥላል ክህደትም ነው። ማንም ሰው ሰአጉል ግብዝነት ራሱን አሳልፎ ከሠጠ መሠረት በሌለው ነገር ጊዜውን በከንቱ ሊያሳልፍ ይችላል። ብዙዎች ባይሆኑ በዚሁ ተጠምደው ለማታለል የሚሞክሩ ጥንትም እንደነበሩ ይነገራል። ነገር ግን የዘመናችን ያህል አልበዙም። በከተሞች አካባቢ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ይህ የማስመሰል ተግባር እየጎላ መምጣቱ የሚነገርለት ካለፉት ሃምሳና አርባ ዓመታት ወዲህ ነው ።

## ቅኔ በኢትዮጵያውያን አድባራትና ገዳማት

በቤተክርስቲያን የተለየ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት ቅኔ ከመንፈሳዊ አገልግሎቶች አንዱ ከሆነ ጀምሮ የተለያዩ የአቀራረብ ዘርፎች ተዘጋጅተውለታል። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አድባራትና ገዳማት ይታወቁባቸው ከነበሩት የመንፈሳዊ አገልግሎት ክፍሎች አንዱ ቅኔ ነው። የአንዱ ደብር ወይም ገዳም ክብረ በዓል በተከበረ ቁጥር በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ገዳማትና አድባራት የክብረ በዓሉ ተካፋዮች ይሆናሉ። የተለያየ የአገልገሎት ድርሻም ይኖራቸዋል። ለነሱ ማለትም የቅዳሴ የንሽ፣የምራትና የቅኔ አገልግሎቶች ለነሱ ይሠጣሉ። ለማስረጃም ያህል የሕዳር ጽዮን በዓለ ንግሥ በአክሱም ሲከበር የዋዜማው ቅኔ ከነቅዳሴው ለደብረዳሞ የዕለቱ ቅዳሴ ለደብረሊባኖስ ቅኔው ለነመርጡለማርያም ወይም ለተድባበ ማርያም ሊመደብ ይችላል። በሚሠጠው አገልግሎት ገዳሙን ወክለው የሚላኩት ግለሰቦች አይነቀፉም ወይም አይመሰገኑም ነቀፋውም ሆነ ምስጋናው የሚሠነዘረው ለላካቸው ገዳም ወይም ደብር ነው። ምክንያቱም ተወካዮቹ ራሳቸው እንደፈለጉ የተላኩበትን የአገልግሎት ዘርፍ አያከናውኑም ነበር መመሪያ ይሠጣቸዋል። ይልቁንም ቅኔን በተመለከተ ልዩ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር። ሌሎቹ የአገልግሎት ዓይነቶች በየዓመቱ አይለወጡም ቋሚዎች ናቸው። ቅኔ ግን



www.ethiopianorthodox.org

ሁልጊዜ አዲስ እየሆነ ነው የሚቀርበው በመሆኑም ልዩ ዝግጅት ይደረግበት ነበር።

በደብሩ ወይም በገዳሙ የሚገኙ መምህራን ተወያይተው ቅኔውን ያቀነባብሩታል። ያ በጉባኤ የተዘጋጀው ቅኔ ለተወካዮቹ ይሠጣል። ተወካዮቹም በተላኩበት ቦታ ስም የተሠጣቸውን ቅኔ ያበረክታሉ። ስለዚህ የተወካዩ ስም ተጠቅሶ እገሌ ይህን ቅኔ ተቀኘ አይባልም ነበር። የዕገሌ ደብር ወይም ገዳም ካህናት የተቀኙት ቅኔ ተብሎ ይጠቀስ ነበር እንጂ። ያ በብዙ መምህራን የሚዘጋጀው ቅኔ በትምሕርት ሰጭነቱና በንባቡ አሰካክ እንዲሁም በምሥጢሩ ለተተኪው ትውልድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ተሐድሶ የሚሰጥ ነበር።

ይህ ዓይነቱ ዝግጅት የቀረበት ዘመን ባይታወቅም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ እንደሆነ ይገመታል። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ገዳማትና አድባራት ይገኙ የነበሩ ካህናት በሙሉ የተሟላ ዕውቀት ነበራቸው። በማንኛውም የቤተክርስቲያን ትምሕርት የበሰፀገ ዕውቀት ሳይኖራቸው ወደገዳም አይገቡም ነበር። ምንኩስናም አይፈቀድላቸውም የአድባራት አገልጋዮችም እንዲሁ በሁሉም የቤተክርስቲያን ትምህርት የጠለቀ ዕውቀት መኖር ከላይ ለተጠቀሰው የሕብረት ዝግጅት ዓይነተኛ ምክንያት ነበር።

በቤተክርስቲያን ሞያ ብዙ ለውጥ ታይተዋል በብዙ ጥረት ከፍተኛ የቤተክርስቲያን ትምሕርት ባለቤት መሆን በተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ ተወስኖ ቀርቷል። ባንዱ ገዳም ወይም ደብር በቂ ዕውቀት ያላቸው መምህራን ማግኘት እንደብርቅ ታየ። ብዙ መነኩሳት ወይም ብዙ ካህናት ቢኖሩም ምንም ትምሕርት የሌላቸው ናቸው። ስለዚህ ገዳማቱንና አድባራቱን የሁከትና የብጥብጥ መድረኮች እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል። ሰላም ሰፍኖባቸው የሚገኙ እጅግ ጥቂቶች ናቸው። በነዚህ ቦታዎች ሰላም መጥፋት የቤተክርስቲያንን ምሑራን አርቋል። ኢትዮጵያውያን መምህራን በገዳም ወይም በደብር ከመቀመጥ ይልቅ በገጠር መቀመጡን ይመርጣሉ አልፎ አልፎ ግን በየአድባራቱና በየገዳማቱ ለመቀመጥ የመረጡ ምሑራን አልታጡም።



ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የሊቃውንት ጉባዔ ያዘጋጀው ቅኔ በተወካይ ተልኮ በክብረ በዓላት በላኪው ቦታ ስም መነገሩ የቀረው። ከላይ እንደተገለፀው አንዳንድ ምሑራን በግድም ይሁን በውድ በገዳማትና በአድባራት ይኖሩ ነበር። እነዚህ ምሑራን በግላቸው ያዘጋጁትን ቅኔ ይቀኙ ጀመር ስለሙ ለክብረ በዓል ሲላኩ ያሉበትን ቦታ ወክለው ነው ቅኔው ግን የግላቸው ይሆናል። በዚህ መሠረት በጉባዔ ቅኔን ማቀነባበር እንደትልቅ ነውር ተቆጠረ። አብዛኛው የሚነገረው ቅኔ ፖለቲካዊ ነው ወይም ደግሞ የግል ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ኑሮ ችግር መግለጫ ሆኗል ትምህርት ሰጭነቱና እግዚአብሔርን የማምለክ መግለጫነቱ ጨርሶ ተረስቷል።

ብዙዎች ቅኔን ያውቃሉ ከተባሉ ማንም ጠያቂ እንደሌላቸው ስለተረዱ ወድያውኑ ከመቅጽበት ቅኔን ያወርዱታል እንዲባሉ የሆነውንና ያልሆነውን መቀባጠር የዘወትር ተግባራቸው አድርገውታል። ወዲያና ወዲህ እየተወራጩ ማጠን የሌለው ጩኸታቸው ሲያስተጋቡት አእምሮ ያለው ያዝናል ይተክዛል የነሱ ቢጤ የሆነው አእምሮ ቢስ በጩኸታቸውና በመዝለላቸው ብቻ አድናቆቱን በጋለ ጭብጨባ ይገልጽላቸዋል።

17ኛው ክፍለዘመን የጎንደር አድባራት ካህናት በሕብረት አዘጋጅተው ያቀረቡት ቅኔ ባንድ ሰው እንዲቀርብ ያደርጉ እንደነበር የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች አሉ። ከማስረጃዎቹ አንዱ በእቴጌ ምንትዋብ ዘመን የተፈፀመው ይገኛል። በዘመኑ የጎንደር ርዕሰ አድባራት ደብረብርሃን ሥላሴ ነበር ፲ ነገር ግን እቴጌ ምንትዋብ ግብር ባስገቡ ጊዜ የደብረብርሃን ካህናት በቅድሚያ ሳይሆን ዘግይተው እንዲገቡ ተደረገ። እነሱም ስለተፈፀመው ስህተት በግብዣው ላይ ለመግለፅ አንድ ሥላሴ ቅኔ አዘጋጅተው /በሕብረት/ ከመካከላቸው የተመረጠው አንባቢ እንዳያነብ አድርገዋል። ቅኔው ቀጥሎ ያለው ነው። "ርዕሰ ደብረብርሃን ዕግረኮነ ውስተቤትኪ ንግሥተ ነጋሢ ዮሐንስ ነጋሢ ዘአውረሰኪ መንበረ"

እስመ የም ዕደፅዋኤሁ ድሕረተ ተአሥረ፣
እንዘኢይሠርቅ ምንተ ጥሪተ ሐሰት ነሡረ፣



www.ethiopianorthodox.org

ዝንቱስ ግፍዕ እመተነግረ ፣ ዓዕይንት ይስምዓ ኵሎ
ነገረ ወአእዛን ይርአያ አድባረ

ይህ ቅኔ በግለሰብ ስም ሳይጠቀስ የደብረብርሃን ሥላሴ ካህናት ቅኔ እየተባለ ይነገራል።

እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ እንደመጣው ስመጥር የቅኔ መምህራን አልጠፉም ነበር መምሕር ገብረሕይወት፣መምሕር፣ዕፁብ መምሕር ገብረመድሕን፣ መምሕር ብዙአየሁ ከነሱ የሚጠቀሱ ናቸው። ከነሱ ባንዱ የመማር ዕድል የገጠመው ሁሉ የግዕዝን ሂደት ሊረዳ ይችላል።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መካከል ዘግይተው በሞት የተለዩት መምህር ዕፁብ ናቸው። መምሕር ዕፁብ በዋድላ፣በጎጃምና በጎንደር እየተዘዋወሩ ለ50 ዓመታት ያህል ቅኔን አስተምረዋል። እኒሁ ሊቅ በትርጓሜ መጻሕፍትና በያሬዳዊ ዜማ ይህ ቀረህ የማይባሉ ነበሩ። ከሚቀኟቸው ቅኔዎች ምሥጢር ብቻ ሳይሆን የግዕዝን ሰዋሰው መማር ይቻላል። የቅኔው አሰካክ እጅግ ያስደንቃል አጣጣሉና ንባቡ የጥንታዊቷን ቤተክርስቲያን ትዝታ በተመስጦና በዓይነሕሊና እንድትጎበኝ ያስችላል።

ብዙ ሰዎች በጎጃም በሸዋ በጎንደር አካባቢና በሌሎችም በቅኔ መምሕርነት ተመድበው ብዙ ዓመታትን ካሳለፉ በኋላ ከያሉበት ቅኔያቸው ይደርሳቸውና የንስሐ ያህል "..ለካስ ራሳችንን በራሳችን ስናታልል ኖረናል" እያሉ ያሳለፉትን ጊዜ በፀፀት እያስታወሱ በመምጣት እንደገና ወደተማሪነት ይለወጡ ነበር። የመምሕር ዕፁብና የመምሕር ብዙአየሁ ቦታዎች ቅርበት ነበራቸው። የኔታ ብዙአየሁ አገባብን ያስተምሩ ነበር በዋሸራው የቅኔ መንገድ ስልጥነው ለቅኔ መምህርነት የበቁ ሁሉ ወደ የኔታ ብዙአየሁ እየሄዱ አገባብ ይማሩ ነበር። የኔታ ብዙአየሁ አገባቡን ካስተማሩአቸው በኋላ በቃል የተማሩትን አገባብ በተግባር ለመተርጎም የሚችሉት የመምህር ዕፁብን የቅኔ መንገድ ያውቁ እንደሆን ብቻ መሆኑን ይመክሩአቸው ስለነበር በሳቸው ምክር ብዙዎች ወደ የኔታ ዕፁብ እየሄዱ የቅኔ ዕውቀታቸውን አስፋፍተዋል።

ቅኔን ያህል ሞያ መምህር ዕፁብ በቀላሉ አይመለከቱትም ነበር በማሕሌት ጊዜ ቤተክርስቲያን የሚገቡ



የቅኔ ምሑራን ሁሉ ተጠበው ተጨንቀው ያዘጋጁትን ቅኔ ይዘው እንዲገቡ አጥብቀው ይመክሩ ነበር። ብዙዎች በመመፃደቅ ራሳቸውን ለማወቅ ከማይችሉበት ደረጃ እንደደረሱ ይስተዋላል። ምንም ሳያስቡ ተመሪው ከቀረበ ጊዜ ጀምሮ ብቻ ከመቀጽበት እንደሚያወርዱት ለመምሰል የአሉባልታ ድምፅ ያሰሙሉ ለእግዚአብሄር በሚቀርበው ምሥጋና ላይ የራሱን ክብር ብቻ ለማስተዋወቅ መጣር ምንኛ ስህተት መሆኑን ብንረዳው በተሻለ ነበር፤ ቅኔ በውስጡ ስብከትን ዶግማንና ሌሎችን የቤተክርስቲያን ምሥጢራትን ያቀፈ ነው፤ በተቻለ መጠን ነቀፋና ትችት እንዳይገባበት መጠንቀቅ ያስፈልጋል ይህ የምሥጋና ክፍል ከቅዱስ መጽሐፍ የመነጨ ነው "..ሰብሕዎ ለእግዚአብሄር ስብሐተ ሐዲሰ.." የሚለው የቅዱስ መጽሐፍ ዐረፍተ ነገር ነው መሠረቱ።

ይህን ሁሉ በመገንዘብ መምህር ዕፁብ ለራሳቸው የከንቱ ውዳሴ መግለጫ የሚያደርጉትን ሰዎች ከመቃወም አልፈው ይገሥፁአቸውም ነበር። የሳቸው ተግሣጽ ዕውነትን ከመመስከር የመነጨ ነው። ራሳቸው በቤተክርስቲያን ሲቀኙ እግዚአብሔርን መፍራት መሠረት አድርገው ስለሆነ የሚቀኙት የተመሠጠ መንፈስ ከፊታቸው አይለይም ነበር። ከሳቸው የተማረ ሁሉ አባባላቸውን ይገነዘበዋል ሌሎች ግን በተቃውሞ መንገድ ነው የሚቀበሉት።

ከተሞች እየበዙ በሄዱ ቁጥር (በኢትዮጵያ) ሰዎች ከገጠር ይልቅ በከተሞች ተሰባስበው መኖርን ይመርጣሉ። አውራ ጎዳናን ተከትለው የንግድ ማዕከላት የሆኑ ቦታዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ከተማነት ሲለወጡ ይታያል። ከከተማ ነዋሪዎች መካከል የተወሰኑ ግለሰቦች በከተማ ሳይሰሩ መኖር እንደሚቻል የሚያምኑ መክሰት የግድ ነው እንደዚህ ያሉ ሰዎች ዞሮ ዞሮ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የአገልግሎት ዕቃዎች (ንዋየ ቅድሳት) ና ማጭበርበራቸው የማይቀር ነው። ንዋየ ቅድሳቱን ከመርካቶ እየገዙ ሕዝበ ክርስቲያኑን ያታልሉበታል። ከዚሁ ጋር ቅኔንም በተሳሳተ መልኩ ይጠቀሙበታል ጥቂት የቅኔን መንገድ ያጠኑ የቅኔ መምህር ነኝ ይላሉ ተባራሪ አንዳንድ የጥንት ቅኔ ሰምተው ከሆነ ቅኔ ተቀኘቻለሁ ወዘተ እያሉ በቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት ሳይቀር በመግባት



www.ethiopianorthodox.org

ያለምንም ፍርሐት የአስመሳይነት ሕይወታቸውን ሲመሩ ይታያል።

ድጓ ቅኔ ነው፣ ሰዓታት ቅኔ ነው፣ ምሕላ ቅኔ ነው፣ቅዳሴም ቅኔ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሠረት በማድረግ በንፁሕ ልቡና እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚፈፀመው ሁሉ ቅኔ ነው።

በግጥም እየቀረፁ የሚያቀርቡት አሽሙር፣ ሽሙጥ፣ ሰውን ማሞገሥ ወይም ማጥላላትና ሌላም ይህን የመሰለ ሁሉ በቅኔ ቦታ ሥፍራ የለውም።




## የግርጌ ማስታወሻ

1. የዮሐንስ ወንጌል 2[illegible]
2. ዘፍ. 16፥[illegible] ዓሞፅ 8፥6
3. ዘፍ. [illegible] ዓሞፅ 8፥6
4. ዓሞፅ 8፥5
5. ድጓ መዋሥዕት [illegible] ተግሣፅ 26 ግንቦት
6. 1ቆሮ. 9፥19
7. መዝሙረ ዳዊት [illegible]
8. [illegible]
9. [illegible]
10. [illegible] ቆሮ. 4፥5
11. [illegible]


www.ethiopianorthodox.org